## ፈጣሪያችንና አምላካችን ኢየሱስ መሲሕ፡
## ከማትለየው፡ ቅድስት እናቱና እናታችን ድንግል ማርያም ጋር፡
## አስቀድሞ፡ ጾመ-ኢትዮጵያን፥ አከታትሎም፡ ዓቢይ-ጾምን አስፈጽሞ፡
## ለዘንድሮው በዓለ-ሆሣዕናና ሰሙነ ሕማማት፡
## እንኳን፡ በደኅና አደረሰን!

# የ፪ሺ፰ ዓመተ ምሕረት
# የሕማማት መልእክትና ሥርዓተ ጸሎት።

---

**ይድረስ**፡- በምድርና በሰማያት በመላችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች፥ ነጋሚዎች እና ካህናት (የአገልግሎት ባልደረቦች)፥ ዜጎችም ኾናችሁ፡ "ኢትዮጵያ" በተባለችው አገር ሠፍራችሁ፥ በዓለሙ አህጉራትም ተዘርታችሁ፡ በቀዳማዊቷ የትንሣኤና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ሕይወት ለምትኖሩ፡ "የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች!" ለኾናችሁት ወገኖቻችን!

በእግዚአብሔርና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ስም፡ ኢትዮጵያዊዉን ሰላምታችንን፡ በያላችሁበት እናቀርብላችኋለን።

ከ"ጾመ ኢትዮጵያ" ጋር ተያይዞ የመጣውን "ዓቢይ ጾምን" (ሁዳዴን)፡ ዓቅማችንና የኑሮ ኹኔታችን በፈቀደልን መጠን፡ በዚያው በጀመርነው፡ በ"ጾመ ኢትዮጵያ" መንፈስና ሥርዓት መቀጠላችን ይታወሳል፤ እንደዚያ አድርገን በመቀጠላችንም፡ መልእክቱንና ሥርዓተ ጸሎቱን፡ ቀደም ባለው ጽሑፋችን፡ በሰፊ ሓተታ ካቀረብነው፡ ከዚህ፡ ከሆሣዕና ሰንበት፡ እነሆ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ልንደርስ ችለናል።

እንግዴህ፡ ዘንድሮ፡ ከሚያዝያ ፲፯ ቀን የሆሣዕና እሑድ ማታ ጀምሮ፡ ጌታችን፡ በዕረፍቱ አክብሮ፡ ዘለዓለማዊት እስካደረጋት፡ እስከሚያዝያ ፳፬ ቀን ዕለተ ሰንበት ማታ፥ ፳፻፰ ዓ. ም. ድረስ ያለው ሳምንት፡ "ሰሙነ ሕማማት" ተብሎ፡ የጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ የመስቀል መከራዎቹ የሚታሰቡበት ሰሞን በመኾኑ፡ የመታሰቢያው ጾም፥ ጸሎቱና ስግደቱ ተጠናክሮ የሚበዛበት፥ ደግሞም፡ የጸሎቱ ዓይነትና የዜማው ስልት፡ ከጾመ ኢትዮጵያውና ከዓቢይ ጾሙ የተለየ መኾኑን ተገንዝባችሁ፡ ቀደም ብለን፡ በጀመርንበትና እስከዚህ ባደረስንበት፡ በዚያ የጾም ይዘት፡ በይበልጥ ተጠምደን፥ በጸሎቱ ጽናትም፡ በይበልጥ ተመስጠን፥ በስግደቱም መጠን፡ በይበልጥ ተጠናክረን እንድናካኺደው እናሳስባችኋለን ።

ስለሳምንቱ ምንነት የሚያብራራውን ሓተታ፥ እንዲሁም፡ የምንባቦቹን ዝርዝርና የዜማዎቹን ቅንብር ሸክላ የያዘው፡ የሰሙነ ሕማማት ሥርዓተ ጸሎት፡ እንደሚከተለው፡ በየመልኩ ተዘጋጅቶላችኋልና፡ ተከታተሉት! "ሰሙነ ሕማማትን፡ በመልካም አከናውነን፡ ከምናበረክትላቸው የንስሓ ፍሬአችን ጋር፡ ለብርሃነ ትንሣኤው እንደሚያበቁን የምናምናቸው ቅድስት ሥላሴ ይመስገኑ!" እያልን፡ ይህንኑ መርሓ ግብር፡ እየከፈታችሁ ትጠቀሙበት ዘንድ፡ ይኸው አቅርንበንላችኋል።

# ሰሙነ ሕማማት

ከዕለተ ትንሣኤ በፊት፡ ከሆሣዕና እሑድ ማታ፡ "**ዘአክበራ፥ ወአልዓላ እግዚእነ በዕረፍቱ፥ ወዘገብረት ዘለዓለማዊት!**" ማለትም፡ "**ጌታችን፡ በዕረፍቱ፡ አክብሮና አልቆ፡ ዘለዓለማዊት አደረጋት!**" እስከተባለላት፡ እስከዕለተ ሰንበት ማታ ድረስ ያለው ሰሞን፡ "**ሰሙነ ሕማማት**" ይባላል።

አምላካችና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ እኛን፡ ሰዎችን፡ ከዲያብሎስ ገዢነት፥ ከኃጢኣት ቀንበርና ከሞት ፍዳ ሊያድነን፡ ራሱን፡ ለፍጥረቱ ቤዛ አድርጎ በመሠዋት፡ በተለይ፡ ከምሴተ ሓሙስ (ከሓሙስ ማታ) ጀምሮ፡ የትንሣኤው ብርሃን እስከበራባት፡ እስከእሑድ እኩለ ሌሊት ድረስ፡ የተቀበላቸውን ልዩ ልዩ መከራዎች በማሰብ፡ በግልም ኾነ፡ በማኅበር ተወስነን የምናሳልፈው ሳምንት ነው፤ ደግሞም፡ እየራሳችንን፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፡ የእርሱ ሥቃይ ተካፋዮች በማድረግ፡ በፍጹም ትሕትናና ንስሓ፥ በተለየ ጾምና ጸሎት፥ በብዙ ስግደትና በእርሱ ፍቅር ተጠምደን የምንሰነብትበት ስለኾነ፡ "ሰሙነ ሕማማት"፥ ወይም፡ "የኢየሱስ መከራዎች መታሰቢያ ሳምንት" ተብሏል።

ይህ ሳምንት፡ እርሱ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በአስቆሮታዊው ይሁዳ መሪነትና ጠቋሚነት፡ በአይሁድና በሮማውያን ወታደሮች ተይዞ፥ የፊጥኝም ታሥሮ፥ በዕለተ ዓርብ፡ በአደባባይ ሲንገላታ ከዋለ በኋላ፡ ተገርፎና ዕርቃኑን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ፡ የሾህ አክሊልን ከተቀዳጀው ራሱና በጦር ከተወጋ ጎኑ፡ ደሙን ያፈሰሰበት፥ በመጨረሻም፡ "ተፈጸመ!" ብሎ፡ በሰውነቱ፡ የሞት ጽዋን የተቀበለበት ነው። በዚያ አካለ ሥጋውም፡ ወደመቃብር ወርዶ፡ በሥነ ፍጥረት ዝግጅቱ ጊዜ፡ ራሱ የሠራትን ዕለተ ሰንበቱን፡ በዕረፍቱ ሲያከብራት፡ በአካለ ነፍሱ ደግሞ፡ ወደሲኦል ወርዶ፡ ላመኑበት ነፍሳት፡ ነጻ የመውጣታቸውን ምሥራች የሰበከበት ነው።

ከደስታ በፊት፡ ፈተና መኖሩ፥ እንዲሁም፡ ያለመከራ ጸጋ፥ ያለድካም ዋጋ የማይገኝ መኾኑን እንዳንዘነጋ፡ እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የሕማማትን ሳምንት፡ በተለየ ጥልቅና ጥብቅ መንፈሳዊ ሥርዓት እናሳልፈዋለን፤ ፋሲካውን፡ በታላቅ ጉጉት፥ የትንሣኤውንም በዓል፡ በጥልቅ ስሜት እንድንጠብቀው የሚያደርገን፡ ይኸው ይዘታችን ነው። አዎን! እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በጾመ ፍልሰታ፡ ለቃል ኪዳን እናታችን፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፥ በሰሙነ ሕማማት ደግሞ፡ ለቃል ኪዳን አባታችን፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የምንገልጸው የፍቅር ስሜት፡ ሰው ለኾነው አምላክና እርሱን ለወለደችው እናቱ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ ያለን ፍቅር፡ ፍጹም መኾኑን ያስረዳል።

እነዚህ፡ የሰሙነ ሕማማት ቀኖች፡ ለእኛ፡ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች፡ በኢትዮጵያ ላሉትና በምድር ላይ፡ በያለበት ለተበታተኑት ወገኖቻችን፥ ለአገራችን፥ እንዲሁም፡ እኒሁ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ወገኖቻችን ለሚኖሩባቸው አህጉር፥ ለመላውም ዓለም ደኅንነትና ሰላም የምንጸልይባቸው፥ ከፈጣሪያችንም ጋር ያለንን ሕያው ቃል ኪዳን የምናጠናክርባቸው ናቸው።

ሰሙነ ሕማማትን፡ ከጾመ አርብዓ ቀጥለን የምንጾመው፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ መሲሕ ተጠምቆና የአርባ ቀኖች ጾሙን ፈጽሞ፡ በትምህርቱና በተአምራቱ፡ ማንነቱን ካሳወቀ በኋላ፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን፡ የመጨረሻውን የቤዛነት ዓላማውን፡ በመከራና በሥቃይ የፈጸመባቸው ዕለታት የሚገኙባት ሳምንት በመኾኗ፡ ያን እውነታ ለማዘከር ነው።

እውነተኛው መምህር፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለሕዝቡ ከተናገራቸው ቃላት መካከል፡ **"ወአንሰ፡ በእንተ ዝንቱ ተወለድኩ፤ ወእንበይነ ዝንቱ መጻእኩ ውስተ ዓለም፡ ከመ እኩን ሰማዕተ፡ በጽድቅ፤ ወኵሉ ዘእምጽድቅ፡ ውእቱ፡ ይሰምዐኒ ቃልየ። ...አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም። ...ወዝ ውእቱ ኵነኔሁ፤ እስመ ብርሃን መጽአ ውስተ ዓለም፤ ወአብደረ ሰብእ፡ ጽልመተ፡ እምብርሃን፡ እስመ እኩይ ምግባሩ። እስመ ኵሉ፡ ዘእኩይ ምግባሩ፡ ይጸልእ ብርሃነ፤ ወኢይመጽእ ኀበ ብርሃን፡ ከመ ኢይትከሠቶ ምግባሩ፤ እስመ እኩይ ውእቱ። ወዘሰ፡ ጽድቀ ይገብር፡ ይመጽእ ኀበ ብርሃን፡ ከመ ያስተርኢ ምግባሩ፤ እስመ በእንተ እግዚአብሔር ይገብር።"**

ማለትም፡ “እኔ፡ ለእውነት ልመሰክር ተወልጃለሁ፤ ስለዚህም፡ ወደዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የኾነ ኹሉ፡ ድምፄን ይሰማል። ...እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ። ...ብርሃን ወደዓለም ስለመጣ፥ ሰዎችም፡ ሥራቸው ክፉ ነበርና፥ ከብርሃን ይልቅ፡ ጨለማን ስለወደዱ፡ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉን የሚያደርግ ኹሉ፡ ብርሃንን ይጠላልና፤ ሥራውም እንዳይገለጥ፡ ወደብርሃን አይመጣም። እውነትን የሚያደርግ ግን፡ ሥራው፡ በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደኾነ ይገለጥ ዘንድ፡ ወደብርሃን ይመጣል።” የሚለው ይገኛል። (ዮሐ. ፫፥ ፲፱-፳፩፤ ፰፥ ፲፪፤ ፲፰፥ ፴፯)

እንዲህ እያለ የመጣባቸውን እርሱን፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ የአይሁድ ካህናት አለቆችና ሊቃውንት፥ የሕዝቡም ሽማግሌዎች፡ ሥልጣናቸውን፥ ክብራቸውንና ጥቅማቸውን፡ ይጠብቁበት የነበረው፡ ሰው ሠራሽ ሥርዓታቸው ሊፈራርስባቸው መኾኑን ከተገነዘቡበት ጊዜ ጀምሮ፡ ጽኑ ቅንዓት አድሮባቸው፡ በተንኰልና በሓሰት አስይዘው፥ በኣረማውያኑ ሮማውያን እጅ ሊያስገድሉት፡ ምክንያት ሲፈልጉ ቆይተው ነበር።

ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘለዓለማዊው የጽዮን ንጉሥ በመኾኑ፡ እንደነቢያት ቃል፡ **"ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት! ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር! ሆሣዕና በአርያም!"** ማለትም፡ “ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ! በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ፡ ቡሩክ ነው! ሆሣዕና በአርያም!” የሚለውን የምስጋና ቃል፡ ከደቀ መዛሙርቱና ዘንባባ ይዘው ከተከተሉት ሕዝብ፥ ከሕፃናትና ከድንጋዮች ሳይቀር እየተቀበለ፡ በአህያዋና በውርንጫዋ ላይ ተቀምጦ፡ በፍጹም ትሕትና፡ ወደኢየሩሳሌም ከገባ በኋላ፡ **"ቤትየሰ፡ ቤተ ጸሎት ይሰመይ! ወአንትሙሰ፡ ረሰይክምዎ፡ በአተ ፈያት ወሰረቅት!"** ማለትም፡ “ቤቴ፡ 'የጸሎት ቤት' ትባላለች!፡ ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን፡ የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት!” ብሎ፡ ቤተ መቅደሱን፡ የገንዘብ መሰብሰቢያ መደብር ያደረጉትን ሰዎች፡ ከነዕቃቸውና ገበታቸው፡ በሥልጣኑ ባስወጣበት ዕለት፡ ያ፡ የቅንዓታቸው ጽዋ ሞላ። (ማቴ. ፳፩፥ ፱-፲፫።)

የአይሁድ ካህናት አለቆችና ሊቃውንት፥ የሕዝቡም ሽማግሎች፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ የት፥ በምን ሰዓትና እንዴት እንደሚይዙት፡ ከዚያች ዕለት አንሥተው፡ ይዶልቱ ጀመር፤ ሰኞና ማግሰኞ ተመካክረው፡ ረቡዕ፡ ነገራቸውን ቀረጡ። እንዲያሲዛቸውም፡ ከአስቆሮቱ ይሁዳ ጋር፡ በሰላሣ ብር ተስማሙ።

ከኹለቱ፡ ማለትም፡ ከሳምንቱ፡ የረቡዕና የዓርብ ጾመ ድኅነት ዕለታት መካከል፡ የመጀመሪያዋ የኾነችው፡ "ረቡዕ"፡ የምትጾመው በዚህ ምክንያት ነው፤ ተከታይዋ "ዓርብ" በስቅለቱ ምክንያት እንደምትጾም ኹሉ።

## ፩. ጸሎተ ሓሙስ/ምሴተ ሓሙስ/የሓሙስ ምሽት፡

ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በተቃዋሚዎቹ ተንኰልና ኃይል ተይዞ፡ ወደሊቃነ ካህናቱ ሸንጎና ወደሮማውያን የፍርድ አደባባይ የሚቀርብበት ጊዜ እንደደረሰ ዐውቆ፡ ቅዱሳን ሓዋርያቱን፡ ለመጨረሻዋ የፋሲካ ራት ሰበሰባቸው፤ ያችም ዕለት፡ "ጸሎተ ሓሙስ"፡ ወይም "ምሴተ ሓሙስ"፡ ማለትም፡ "የሓሙስ ምሽት" በሚል ስያሜ የምትታወቀው ናት። የምሥጢራተ ቍርባንንና ክህነትን ሥርዓታት የመሠረተባትና ያስተማረባት፥ ያሳየባትና የፈጸመባት፥ ከሓዋርያቱም ጋር የመጨረሻውን የኅብረት መዝሙርንና ጸሎትን ያደረገባት ስለኾነች፡ "ጸሎተ ሓሙስ" ማለትም፡ "የሓሙስ ጸሎት" ተብላ ትዘከራለች።

በዚያች ራት ላይ፡ በኦሪቱ የአይሁድ ሕግ መሠረት ሲካኼድ የቆየውን፡ የብሉዩን (አሮጌውን) ኪዳን የፋሲካ በግ ሥርዓት፡ ለመጨረሻ ጊዜ ፈጸመ፤ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ቃል ኪዳን ምክንያት፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ተጠብቆ እየተካኼደ የቀጠለው፡ የኅብስተ አኰቴቱና የጽዋዓ በረከቱ ዘለዓለማዊ ሥርዓት፡ ለአዲሱ ኪዳን የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ ቁርባን ይውል ዘንድ አጽድቆ አጸናው፤ ምሥጢራትን ገለጸ፤ ስለአገልግሎትና ስለትሕትና፡ መመሪያዎችን ሰጠ፤ በአርአያነትም አስተማረ። ይኸውም:-

- ሲበሉ፡ ኅብስቱን አንሥቶ፥ ባርኮና ቆርሶ፡ "**እንክሙ! ብልዑ! ዝ ውእቱ ሥጋየ!**" ማለትም" "**ይህ ሥጋዬ ነው፤ እንካችሁ ብሉ!**"፥ ጽዋውንም አመስግኖ፡ "**ስትዩ እምኔሁ ኵልክሙ! ዝ ውእቱ ደምየ፡ ዘሓዲስ ሥርዓት፡ ዘይትከዐው በእንተ ብዙኃን፡ ለኅድገተ ኃጢአት!**" ማለትም፡ "**ስለብዙዎች፡ ለኃጢኣት ይቅርታ የሚፈስስ፡ የአዲስ ኪዳን ደሜ፡ ይህ ነው፤ ኹላችሁ ከእርሱ ጠጡ!**" ብሎ፡ የቅዱስ ቍርባንን ምሥጢርና ሥርዓት፥

- እግራቸውንም በማጠብ፡ "**እስመ አርአያየ ወሀብኩክሙ፡ ከመ ትግበሩ አንትሙኒ፡ በከመ ገበርኩ ለክሙ አነ።**" "ማለትም፡ "**እኔ፡ ለእናንተ እንዳደረግሁ፡ እናንተ ደግሞ፡ እንዲሁ ታደርጉ ዘንድ፡ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ!**" ብሎ፡ የትሕትና አገልግሎትን፥

- በኑዛዜውም ቃል፡ "**ወእሁበክሙ፡ ሐዲሰ ትእዛዘ፡ ከመ ትትፋቀሩ በበይናቲክሙ፡ በከመ አነ አፍቀርኩክሙ፡ ከማሁ፡ አንትሙኒ ተፋቀሩ በበይናቲክሙ! ወበዝንቱ፡ የአምረክሙ ኵሉ፡ ከመ አርዳእየ አንትሙ፡ እምከመ ተፋቀርክሙ በበይናቲክሙ።**" ማለትም፡ "**ደቀ መዛሙርቴ እንደኾናችሁ፡ ሰዎች ኹሉ ያውቁ ዘንድ፡ እርስ በእርሳችሁ እንድትዋደዱ፡ እነሆ፡ አዲስ ትእዛዝን ሰጥቻችኋለሁ!**" ብሎ፡ ፍቅርን፥

- በጌቴሴማኒ ተይዞ ከመታሠሩ በፊት፡ "**ትግሁ ወጸልዩ ከመ ኢትባኡ ውስተ መንሱት! እስመ መንፈስ ይፈቱ፤ ወሥጋ ይደክም።**" ማለትም፡ “**ወደፈተና እንዳትገቡ፥ ትጉ! ጸልዩም! መንፈስስ ተዘጋጅታለች፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው፤**” ብሎ፡ በሃይማኖት ቆራጥ ኾኖ፡ በጸሎት መትጋትን፡ ራሱ ፈጽሞ÷ ለእነርሱ በማሳየት ነው። (ማቴ. ፳፮÷ ፳፮-፳፰፤ ፵-፵፩። ዮሐ. ፲፫÷ ፲፪-፲፯፤ ፴፬-፴፰።)

ሰሙነ ሕማማት፡ ይህን ምሥጢሩን ዐውቀን÷ ሥርዓቱን ተቀብለንና ትእዛዙን አክብረን÷ አርአያነቱንም ተከትለን የምንኖር መኾናችንን የምንመረምርበት÷ ለእየራሳችንም ኾነ፡ ለእርሱ፡ በግብር ፈጽመን የምናሳይበት ሳምንት ነው።

ከሕማማት ሰኞ፡ እስከጸሎተ ሐሙስ፡ በጾም ተወስነን፡ በቤተ ክርስቲያን÷ ወይም፡ በእየቤታችን የምናካኺደው፡ የጸሎት÷ የስግደት÷ የኀጽበተ እግርና የቅዳሴ ሥርዓት÷ በጸሎተ ሐሙስ ማታ የሚዘረጋው ገበታ÷ በዚያም፡ የምንሳተፈው ኅብስት (ዳቦው)፡ ይህን የኦሪቱን የፋሲካ ቂጣ ያስታውሰናል። በተለይም፡ “ጉልባን”፡ ተብሎ የሚዘጋጀው ንፍሮ፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ከጌቴሴማኒ የተክል ቦታ ጀምሮ፡ እስከመቃብሩ ድረስ፡ በተቀበላቸው የተለያዩና የበዙ ታላላቅ መከራዎች፡ የሥጋው አካል፡ እንደዚህ፡ በእሳት እንደሚከከው ቅይጥ እህል፡ መጐሣቈሉን ለማዘከር፡ በአንክሮ የምንቀምሰው፡ ምግብ ነው።

## ፪. ዕለተ ዓርብ - ስቅለት፡-

ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ሐሙስ ማታ ተይዞ÷ የአይሁድ ሊቃነ ካህናት÷ ሊቃውንትና የሕዝቡ ሽማግሌዎች፡ በሸንጓቸው ተሰብስበው፡ ሌሊቱን ሙሉ፡ ሲከስሱትና ሲወቅሱት ካደሩ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በመስቀል ስቅላት እንዲቀጣ፡ የበኩላቸውን ፍርድ ሰጥተው፡ ለፍርዱ አፈጻጸም፡ ወደሮማዊው ገዢ፡ ወደጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት። አረማዊው ጲላጦስም፡ ምንም እንኳ፡ የሞት ፍርድ እንዲፈጽምበት፡ “ወንጀለኛ” ተብሎ፡ የቀረበለት፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከሚነገርበት ክስና ውቅስ ኹሉ፡ ፍጹም ንጹሕ መኾኑን ቢያረጋግጥም÷ ከዚህም የተነሣ፡ "**ንጹሕ አነ እምደሙ፡ ለዝ ብእሲ ጻድቅ!**" ማለትም፡ “**እኔ ከዚህ እውነተኛ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ!**” ብሎ፡ እጆቹን፡ በአደባባይ ቢታጠብም÷ በምንም መንገድ ሊያድነው ባለመቻሉ፡ በግፍ ይሰቅሉት ዘንድ፡ "**ደሙ ላዕሌነ÷ ወላዕለ ውሉድነ!**" ማለትም፡ “**ደሙ፥ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይኹን!**” ላሉት ከሳሾቹ፡ መልሶ ሰጥቷቸው ገደሉት፤ አስገደሉት። (ማቴ. ፳፯÷ ፲፱-፳፮።)

ይህ ኹሉ የኾነው፡ ጲላጦስ፡ ኢየሱስ መሲሕን ሊለቅቀው ፈልጎ፡ ነገር ግን፡ ከሳሾቹን ለማስደሰት÷ ሥጋዊና ምድራዊ ሥልጣኑንም ለማቆየት ሲል፡ ከሕግ ውጪ፡ በግፍ ካስገረፈውና በዚያ ወቅት፡ በሮማውያን አገዛዝ ላይ ዐምፆ፡ የታሠረውን፡ “በርባን” የተባለውን ነፍሰ ገዳይ፡ በፍርድ አስወግዶ፡ ይኸኛውን ንጹሑን እስረኛ፡ በምሕረት ሊፈታው ሞክሮ፡ ሳይሳካለት ከቀረ በኋላ ነበር።

ጌታ፡ በዕለተ ዓርብ የተቀበላቸው የመስቀል መከራዎች፡ በግፈኛ ወንጀለኛ ላይ እንኳ፡ "ይደርሳሉ!" ተብለው የማይታሰቡ ናቸው፤ ምንም በደል፥ ጥፋትና ኃጢአት እንደሌለበት፡ ከሳሾቹም፥ ፈራጁም፡ ልቦናቸው እያወቀ፡ ይህን ያህል፡ ለምን ጨከኑበት? ይሙት በቃ የተፈረደበት፡ ነፍሰ ገዳዩ በርባን ተፈትቶ፡ የተራብ አጥጋቢና የተጠማ አርኪ፥ አካል አልባሽና ሕሙም ፈዋሽ፥ የእሥራት ፈቺና የባርነት ነጻ አውጪ፥ ሙት አሥነሽና ነፍስ ኣዳኝ የኾነው፡ የሕይወት ጌታ ኢየሱስ መሲሕ፡ "ይሰቀል!" ብሎ መፍረድና ፍርዱን በአስቸኳይ መፈጸም፡ ምን ማለት ነው?

ቅድስት ነፍሱ፡ ከቅድስት ሥጋው ከመለየቷም በፊት፡ ገና፡ በመስቀል ላይ እየተሠቃየ ሣለ፡ የተራቡትን ያጠገበና የተጠሙትን ያረካ፡ ያ፡ ርኅሩኅና ቸር ጌታ፡ በድርቀት የተሰነጣጠቀ ጕረሮውን ለማርጠብ ፈልጎ፡ አንዲት የውኃ ጠብታን ቢጠይቅ፡ ያች፡ የውኃ ጠብታ እንኳ ተነፍጋው፡ መራራ ሓሞትን፡ በሰፍነግ ሞልተው፡ አፉ ላይ መጭመቅ፡ ምን ዓይነት ጭካኔ ነው?

ሰብአዊው ፍጡሩ፡ ለእርሱ፡ ለቸር ፈጣሪውና መልካም እረኛው፡ ሊከፍለው የሚገባው ውለታ፡ ከቶ ይህን የመሰለውን ሊኾን ይገባ ነበርን? አልነበረም። ነገር ግን፡ በክፋት ጠንቅ፡ እንዲህ፡ ከመጨረሻው የጕሥቍልና ዐዘቅት ውስጥ የወደቀውን፡ ይህንኑ፡ ጨካኙን ሰብአዊ ፍጥረት ለማዳን የሚቀርበው ቤዛ፡ በዚህ መልክ ተገልጾ፡ መሠዋት ነበረበት።

ታዲያ፡ ዛሬ ያለነው የሰው ወገኖች፡ "በዚያን ዘመን የነበሩ አይሁድና ሮማውያን፡ በጌታ ላይ እንዲህ አደረጉ!" እንላለን። ይኹን እንጂ፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ "**አማን እብለክሙ! ኵሎ ዘገበርክሙ፡ ለአሓዱ፡ እምእሉ ንኡሳን አኀውየ፡ ሊተ ገበርክሙ፤ ...ዘኢገበርክሙ ለአሓዱ እምእሉ ንኡሳን አኀውየ፡ ሊተ ኢገበርክሙ።**" ማለትም፡ "እውነት እላችኋለሁ! ከኹሉ ከሚያንሱ፡ ከእነዚህ ወንድሞቼ፡ ለአንዱ እንኳ ያደረጋችሁት በጎ ሥራ፡ ለእኔ አደረጋችሁት! ካላደረጋችሁትም፡ ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም!" እንዳለው፡ እኛስ፡ በሌሎች ላይ ምን እያደረግን፥ ወይም እያላደረግን ነን? **ለእነዚህ ጥያቄዎች፡ እያንዳንዳችን፡ በነፍስ ወከፍ፡ ለየግሊናችንና ለእግዚአብሔር መልስ፡ መስጠት አለብን!**

እርሱ፡ እኛን፡ የቃል ኪዳን ወገኖቹን፡ ከዲያብሎስ ገዢነት ነጻ አውጥቶ፥ ከኃጢአት ቀንበር ፈትቶና ከሞት ቍራኝነት አላቅቆ፡ ለዘለዓለማዊው ደኅንነት ያበቃን፡ እንዲህ ባለው፡ የመስቀል መከራዎቹ ስለኾነ፡ "እኛስ፡ ዛሬ፡ እርሱን፡ በፍጹም ፍቅር ወድደነው፥ ድምፁንም፡ በእውነት ሰምተንና ቃሎቹን ተከትለን፡ ከእርሱ፡ በቃል ኪዳን የተቀበልነውን ሃይማኖትና ምግባር እየፈጸምን፡ በከፈተልን ሕይወት እንኖራለንወይ? በእርግጥ፡ እየኖርነው ከኾነ ደግሞ፡ ከዚህ የተነሣ፡ የሚደርስብንን ፈተናና መከራ፡ እንዴት ነው እየተቀበልነው ያለነው?" ብለን፡ እየራሳችንን መመርመር ይኖርብናል።

በዚህ ዓለም፡ በእርሱ አምነውና የእርሱን ፈለግ ተከትለው የሚኖሩ ኹሉ፡ ምንም በጎ ሥራ ቢያደርጉ፡ የሚመለስላቸው ውለታ፡ ይህን የመሰለው ፈተናና መከራ መኾኑን ያውቁታል፤ እርሱ፡ በመስቀል ላይ እየተሠቃየ ሣለ፡ "**አባ! ሥረይ ሎሙ፡ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ!**"

ማለትም፡ “አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና፡ ይቅር በላቸው!” ሲል፡ ያስሰማው የዕርቅ ቃል፡ ዘወትር በጆሮአቸው እየደወለ፥ እንዲሁም፡ "**ወበዓለምሰ፡ ሀለወክሙ፡ ሕማመ ትርከቡ! ወባሕቱ፡ ጽንዑ! እስመ አነ ሞዕክዎ ለዓለም።**" ማለትም፡ “በዓለም ሣላችሁ፡ መከራ አለባችሁ! ነገር ግን አይዟችሁ! እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ!” ብሎ በሰጣቸው ቃል እየተጽናኑ፡ ከክፉዎች ሰዎች የሚመጣባቸውን፡ ማናቸውንም ፈተናና የሚደርስባቸውን መከራ፡ በትእግሥት በመቀበል፡ ተጋድሎአቸውን ይቀጥላሉ፡፡

በተለይ በዕለተ ዓርብ የምንጾመው ጾም፥ የምንጸልየው ጸሎትና የምንሰግደው ስግደት፡ በዚህ፡ በኢየሱስ መሲሕ መንፈስ ካልኾነ፥ ፋሲካችንም፡ እርሱ በመኾኑ፡ የምንፈስከው፡ በዶሮ፥ ወይም፡ በበግ፥ ወይም፡ በበሬ፥ ወይም፡ በሌላ፡ በማናቸውም ዓይነት ሥጋ ሳይኾን፡ በእርሱ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ካልኾነ፡ ድካማችን ኹሉ ከንቱ ይኾናል፡፡

ዓርብ፡ ወደስግደቱ መጨረሻ ግድም፡ ቀሳውስቱ፡ የወይራ ቀምበጥ፡ በቀኝ እጃቸው ይዘው፡ ከቤተ ልሔም ወጥተው ይመጣሉ፡፡ የዚህ ምሳሌ፡ ኖኅ፡ በጥፋት ውኃ ጊዜ፡ የውኃውን ሙላት መጕደልና የምድሪቱ የብስ መታየቱን አረጋግጣ እንድትመለስ፡ ርግብን፡ ከመርከቡ አውጥቶ በላካት ጊዜ፡ የወይራ ቀምበጥ፡ በአፏ ይዛ መጥታ፡ ያበረከተችለትን ምሥራች የሚያስታውስ ነው፡፡ (ዘፍ. ፰፥ ፲-፲፩። ማቴ. ፳፭፥ ፴፩-፵፮፡፡ ሉቃ. ፳፫፥ ፴፬፡፡ ዮሐ. ፲፮፥ ፴፫፡፡)

ቀሳውስቱም፡ በዚሁ መልክ፡ “**በአምላካችን በኢየሱስ መሲሕ የመስቀል መከራ፡ ዲያብሎስ ታሠረ! ኃጢአት ተደመሰሰ! ሞት ተወገደ! የሰው ልጅ ነጻ ወጣ! ከእንግዴህ ወዲህ፡ ሰላምና ደስታ ኾነ!**” እያሉ፡ የምሥራቹን ዜና፡ ለሕዝቡ መናገራቸው ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ምእመን//ምእመኒት፡ የንስሓ ስግደትን በሚሰጡበት ጊዜም፡ ጀርባውን/ጀርባዋን፡ በምሥራቹ የወይራ ቀምበጥ የሚጠበጥቡት፡ “ኢየሱስ መሲሕ፡ አንተን/አንቺን፡ ለኃጢአት ስርየት ያበቃህ/ያበቃሽ፡ እንዲህ ተገርፎና የመስቀል መከራዎችን ተቀብሎ መኾኑን በማስታወስ ስገድ/ስገጂ!” ማለታቸው ነው፡፡

## ፫. ገብረ ሰላም፡-

የሰንበት ፈጣሪዋና ጌታዋ የኾነው ሰላማችን ኢየሱስ መሢሕ፡ በሰውነቱ ሞቶ ሣለ፡ ሥጋውን፡ በመቃብር አሳድሮ፥ ነጻነትንም፡ ለማወጅ፡ በነፍሱ፡ ወደሲያል ወርዶ ያሳለፋት፡ የሰሙነ ሕማማት ሰንበት፡ ሌላ ኹለተኛ ሰንበት ያለች ይመስል፡ አላገባብ፡ "ቀዳሚት" እየተባለች በምትጠራበት ስሟ፡ “ቅዳሜ ስዑር”፥ ወይም፡ "ከሰንበትነቷ የተሻረች ቅዳሜ" ስትባል ኖራለች፤ በዚያን ጊዜ ብቻ፡ የሰንበት ጌታ እርሱ፡ በሥጋው ሞቶ፡ በመቃብር ያሳለፋት ስለኾነች፡ ዕለቷ፡ ከሰንበትነቷ እንደተሻረች በመቊጠር፡ ይህ፡ ልዩ ስያሜ አላገባብ ተሰጥቷት ኖራለች።

እውነቱ ግን፡ ይህ አይደለም። እውነቱማ፡ በዕለቷ የኾነውን መለኮታዊ ድርጊት፡ አስተውለው ሲመለከቱት፡ “ጌታ፡ በመቃብር ውስጥ፡ በሥጋው ያረፈባት በመኾኗ፡ "**ተዘከር፡ ዕለተ ሰንበት፡ ከመ ትቀድሳ!**" ማለትም፡ ‘**የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ!**’ በምትለው፡ በዓሠርቱ ቃላት መሠረት፡ ዕለቲቱን፡ ያከበራት እንጂ፡ ያልሻራት መኾኑ ነው።

ስለዚህ፡ ይኸው፡ "ቅዳሜ ስዑር" የሚለው የተሳሳተ ስያሜ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ አለመኖሩ፡ ሊታወቅ ይገባል። በሌላው ስሕተት ደግሞ፡ "ቀዳሚቷና የብሉይ ኪዳኗ (አሮጌዋ) የአይሁድ" ስትባል የኖረችው፡ ይህችው አንዲቷ ሰንበት ታድሳ፡ "ሰንበተ ክርስቲያን" ስትባል በኖረችው፡ በዘለዓለማዊቷ የአዲስ ኪዳኗ "እሑድ" መቀጠሏን ለማሳየትና ለማረጋገጥ፡ "ተፍጻሚተ ሰንበት" መባሏ፡ አግባብ ይኾናል። (ዘፀአ. ፳፥ ፰-፲፩።)

"ገብረ ሰላመ በመስቀሉ! ትንሣኤሁ አግሃደ!" ማለትም፡- "ጌታ፡ በመስቀሉ፡ ሰላምን አስገኘልን! ትንሣኤውንም በገሃድ ገለጠልን!" እያሉ፡ ካህናቱ፡ በዚህች የሰንበት ዕለት፡ ቈጠማ ይዘው፡ ለሕዝበ ክርስቲያን በማደል፡ ምሥራቹን ያስሰማሉ፤ ያዳርሳሉ።

ይኸው ሳምንት፡ ለጌታ ክብር ስለተሰጠ፡ በሕማማቱ ሰሞን፡ የሙታን፡ ጸሎተ ፍትሓት አይደረግበትም፤ ይህን የመሰለው አገልግሎት፡ ከሕማማቱ አስቀድሞ፥ ወይም፡ ከትንሣኤው ቀጥሎ ባሉት ሳምንታት ይፈጸማል።

እንግዴህ፡ እነዚህ፡ የሰሙነ ሕማማት ቀኖች፡ ለእኛ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች፡ ምን ዓይነቱን፡ የመጨረሻ ፍጹም የተቀደሰ ዓላማ የምናካኺድባቸውና የምንፈጽምባቸው እንደኾኑ፡ እንመልከት!

መነሻው፡ ጌታችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ እናታችንና መድኃኒታችን ቅድስት ሥላሴ ከኾነችው፡ ከድንግል ማርያም፡ በሰውነት በመወለድና በመስቀል መከራው፡ ባስገኘልን ቤዛነቱ፡ <u>እኛን፡ ፍጡራን ወገኖቹን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ፈጽሞ ይቅር ያለን መኾኑን ማመን ነው።</u>

በዚህ መሠረት፡ እያንዳንዳችን፡ በቀዳማዊቷ የትንሣኤና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ሕይወት ለመኖር እንችል ዘንድ፡ በየግል ንስሓችን፡ ስሕተታችንንና ኃጢኣታችንን በማመን፥ የበደሉንንም ኹሉ ይቅር በማለት፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኳችን አማካይነት፡ <u>እየራሳችንን፡ ለፍጹሙ የመንፈሳዊ እውቀትና ህልውና ማዕርግ ማብቃት ነው።</u>

ከዚህ የተነሣ፡ ከጥያቄና ከአቤቱታ፥ ከልመናና ከምልጃ፡ ፈጽሞ ነጻ የኾነ፥ <u>ምስጋናን ብቻ የተመላ ጸሎታችንን ማቅረብ ነው።</u>

አዎን! ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ህልውናዋንና ምስፍናዋን በሚመለከት፡ ሊታወቅ የሚገባው እውነታ፡ በተለይ፡ ካለፈው ነሐሴ ፲፯ ቀን፥ ፳፻፩ ዓመተ ምሕረት ወዲህ፡ ይፋ በወጣው፡ ተከታታይ መለኮታዊ ዐዋጅ አማካይነት፡ የተላለፈው መልእክት፡ ለዓለማውያኑ ሰዎች በይፋ ከተከሠተ ወዲህ፡ ለዚህ ሰሙነ ሕማማት የተመደቡት ኾኑ፡ ሌሎቹ፡ በዓመቱ ውስጥ የምናካኼዳቸው፡ የግልና የማኅበር ጸሎቶቻችን ኹሉ፡ ከጥያቄ፥ ከአቤቱታና ከልመና፡ ወደምስጋና የመሻገር ብቅዓትን እንዲያገኙ የተደረገ መኾኑን፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች፡ በማስተዋል እንድትመለከቱትና በተግባር ላይ እንድታውሉት የምናሳስባችሁ፡ እጅግ ደስ እያለን ነው።

\+ \+ \+

# የሰሙነ ሕማማት ሥርዓተ ጸሎት።

*ከሰኞ እስከ ዓርብ የሚካኼደው፡ ይህ፡ በምንባቦችና በዜማዎች የታጀበ፡ የስግደት ጾምና ጸሎት፡ በግል፥ በቤተሰብ፥ ወይም፡ በማኅበር፡ ከምሽቱ፡ በ፩ ሰዓት፥ ከማታው፡ በ፫ ሰዓት፥ ከሌሊቱ፡ በ፮ ሰዓት፥ ከነግሁ፡ በ፱ ሰዓት፥ ከንጋቱ፡ በ፲፪ ሰዓት፥ ከማለዳው፡ በ፩ ሰዓት፥ ከጧቱ፡ በ፫ ሰዓት፥ በቀትሩ ፮ ሰዓት፥ ከቀትር በኋላ፡ በ፱ ሰዓት፥ በሠርክ፡ በ፲፩ ሰዓት፥ በግእዝ፥ ወይም፡ በኢትዮጵያኛ፥ የዜማው፡ በዜማ፥ አለዚያ፡ በንባብ ብቻ ሊባል፥ ምንባቡም፡ በተካፋዮቹ ተሳትፎ ሊካኼድ ይቻላል፡፡*

*የእየአንዳንዱ ጊዜ የመክፈቻ ጸሎት፡ ካህን/ካህኒት ካሉ በአንዳቸው፥ ከሌሉ፡ ከምእመናኑ/ከምእመናቱ መካከል፡ አረጋዊ/ዊት እና ቀደምት በኾኑት በአንዳቸው ኪዳናዊ ኢትዮጵያዊ/ኪዳናዊት ኢትዮጵያዊት ይመራል፡፡ ተካፋዮቹ፡-*

*- "**እአትብ ገጽየ**" እያሉ፡ አራት ጊዜ በመስገድ ጸሎታቸውን ይጀምሩ፡፡ ስግደቱ፡ ፩ዱ፡ ለእግዚአብሔር፡ ለ፩ነቱ፥ ፫ቱ፡ አብወእምን፡ ፩ ላደረገው፡ ፫ነቱ ነው፡፡*

- **የኢትዮጵያን የሃይማኖትና የቃል ኪዳን ጸሎቶች**፡ *በኅብረት ይበሉ፡፡*

- **"ሰላም ለኪ!"** *ን፡ አንድ ጊዜ ሰግደው፡ ከ*"**ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም**" *ጋር ከጸለዩ በኋላ፡ አያይዘው፡ የዕለቱን* "**ውዳሴ ማርያም**" *በተራ እየተቀባበሉ፥ ከዳዊትም መዝሙር፡ ቢያንስ ቢያንስ አሥር መዝሙራትን ያህል በመድገም፡ ያጠቃልሉ፡፡*

*- ከዚህ በኋላ፡ በኹለት ወገን ኾነው እየተቀባበሉ፡ ከዚህ የሚከተለውን ውዳሴ አምላክ፡ __በግእዝ የዜማ ስልት__ እየዘመሩና* 'አቡነ ዘበሰማያት'*ን እየደገሙ ይስገዱ! እያንዳንዱን ክፍል፡ እንደየዓቅማቸውና እንደየጊዜያቸው መጠን፡ ፫ ፫፥ ወይም፡ ፮ ፮፥ ወይም፡ ፲፪ ፲፪ ጊዜ ሊመላልሱት ይቻላል፡፡*

ለከ ኃይል፥ ክብር ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም፡፡
አማኑኤል አምላክነ! ለከ ኃይል፥ ክብር ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም፡፡
ኦ እግዚእነ ኢየሱስ መሲሕ! ለከ ኃይል፥ ክብር ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም፡፡

ኃይልነ፥ ወጸወንነ፥ ውእቱ እግዚእነ፥ እስመ ኮንከነ ረዳእነ፤ ንብል በአኰቴት፡ "አቡነ ዘበሰማያት! ተቀደሰ ስምከ። መጽአት መንግሥትከ። ኮነ ፈቃድከ፡ በከመ በሰማይ፥ ከማሁ፡ በምድር። ሲሳየነ ዘለለዕለትነ፡ ሀብከነ ዮም። ኅደግከ ለነ፡ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፤ ከመ ንሕነኒ፡ ንኅድግ፡ ለዘአበሰ ለነ። ኢአባእከነ፡ እግዚኦ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅንከነ፤ ወባልሓከነ፡ እምኵሉ እኩይ። እስመ ዚአከ፣ ይእቲ መንግሥት፤ ኃይል፤ ወስብሓት። ለዓለመ ዓለም።

*__ትርጉሙ፡-__*

"ኃይላችን፥ መከታችንና ረዳታችን ለኾንከው፡ ለአንተ፡ ለአምላካችን፡ ለአማኑኤል፥ ለጌታችን ለኢየሱስ መሲሕ፡ ኃይል፥ ክብርና ምስጋና፥ ጽናትም፡ ለዘለዓለም፡ የአንተ ናቸው፡፡" እያልን፡ 'አባታችን ሆይ! በሰማያት የምትኖር! ስምህ ተቀደሰ። መንግሥትህ መጣች። በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ። የዕለት ምግባችንን፡ ለዛሬ ሰጠኸን። ኃጢኣታችንንና በደላችንን ይቅር አልኸን፤ እኛም፡ የበደሉንን፡ ይቅር እንል ዘንድ። አቤቱ፡ ወደፈተና አላገባኸንም፤ ከክፉው ኹሉ፡ አዳንከን፥ ታደግኸን እንጂ። ይህች መንግሥት፥ ኃይልና ምስጋናም፡ የአንተ ናቸው፤ ለዘለዓለሙ። አሜን።' የሚለውን ጸሎት በመድገም፡ እናመሰግንሃለን።"

*ካህኑና ሕዝቡ፡ ስግደቱን፡ እንዲህ እያሉ ይቀጥሉ!*

ለአምላክ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለሥሉስ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለማኅየዊ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለዕበዩ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለዕዘዙ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለመንግሥቱ ይደሉ! ክብር፥ ስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለኢየሱስ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለመሲሕ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለሕማሙ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።
ለመስቀሉ ይደሉ! ክብር፥ ወስብሓት፥ ወዕዘዝ፤ ለዓለመ ዓለም።

*ቀጥሎ ያለውን፡ የመዝጊያ ጸሎት፡ እያዜሙና እየሰገዱ፡ ፫ ጊዜያት ይመልሱት!*

ለከ ይደሉ ኃይል፥ ለከ ይደሉ ስብሓት፥ ወለከ ይደሉ አኰቴት፥ ኦ እግዚእነ ኢየሱስ መሲሕ፤ ለዓለመ ዓለም።

**ትርጉሙ**

"ለአንድ አምላክነቱ፥ ለሦስትነቱ፥ ለሕይወትነቱ፥ ለጽናቱ፥ ለመንግሥቱ፥ ለመድኃኒትነቱ፥ ለመሢሕነቱ፥ ለተቀበላቸው መከራዎቹና ለመሰቀሉ፡ ክብርና ምስጋና፥ ጌትነትም ይገባዋል! ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ ሆይ፥ ለአንተ፡ ኃይልና ክብር፥ ምስጋናም ይገባሃል፤ ለዘለዓለሙ።"

*ከዚህ በኋላ፡ እንደጊዜውና እንደኹኔታው አመቺነት፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት፥ ከሃይማኖተ አበውና ከሊቃውንት፥ ከተአምራትና ከድርሳናት፡ ከሰኞ እስከዓርብ፡ ለሳምንቱ ዕለታትና ጊዜያት፡ የተዘጋጁትን ምንባቦችና ምስባኮች፡ እንደግብረ ሕማማቱ ሥርዓት እያወጡ ማንበብና ማዜም ይቻላል። አስፈላጊው ግን፡ በዚህ ዝግጅት ውስጥ ተካትቷል።*

*ከቅዱሳት መጻሕፍት የተውጣጣውና ከሰኞ እስከዓርብ ያለው፡ የየዕለቱ ምንባቦችና ምስባኮች ዝርዝር፡ በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ላይ ተከናውኖ ስለቀረበ፡ ሥርዓተ ጸሎቱ፡ በዚያ ዝርዝር መሠረት ይካኼዳል።*

*ምንባቡ እንዳበቃ፡* **"ጽንዓ ዛቲ"** *የሚለው፡ ስለሌሎች የሚቀርበው ምስጋና፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ በጸሎቱ መሪ፡ በንባብ ይሰማ! ዲያቆኑ፡ በየምዕራፉ፡ ቃጭል ይደውል! ሕዝቡም፡* **"እቤቱ፡ ይቅር እልከን!"** *የሚል ትርጉም ያለውን፡* **'እግዚኦ ተሣሃልከነ!"** *የሚለውን ተሰጥዎ፡ በዜማ እየተቀበሉ ይስገዱ! ጸሎቱን፡ ለጊዜያቱ መከፋፈልም ይቻላል።*

*የጸሎቱ መሪ፡-* ስለዚኺ ቦታ መጽናት፥ በቅዱሳንና በቅዱሳት ስም ስለሚጠሩም ቦታዎችና ገዳሞች፥ በውስጣቸውም ስለሚኖሩ ኹሉ፥ በጠቅላላም፡ ስለዚህ ዓለም መጠበቅ አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ከክፉ ኹሉ ስለጠበቃቸው። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* በዚች ቦታና በሌሎችም ቦታዎች ስለሚገኙ፡ በነፍስ በሥጋ ታምመው ስለተፈወሱ ኹሉ አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ለእነርሱም፥ ለእኛም፡ ሕይወቱን፥ ጤንነቱን ሰጥቶ፡ በጎ ነገርን ስላደረገልን፡፡ የእኛንም ኃጢአታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* በባሕር፥ በየብስ፥ በአየር፥ በወንዝ፥ በቀላይ፥ በሌላውም መንገድ ኹሉ ስለሚጓዙ ሰዎች አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ በቀና መንገድ መርቶ፡ በሰላም፥ በደስታ፡ ወደመኖሪያቸው ስለመለሳቸው። የእኛንም ኃጢአታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ከእርሻ ስለሚገኝ ፍሬ፥ ስለዛፎችና ስለወይኖች፥ በዓለምም ውስጥ ፍሬን ስለምታፈራ ዛፍ ኹሉ አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ባርኮ፥ አብዝቶ፥ ከጥፋትም ጠብቆ፡ ለፍጻሜ ፍሬ ስላደረሳቸው። የእኛንም ኃጢአታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* አምላካችን ክርስቶስ፡ በገዦችና በፈራጆች ፊት፡ ይቅርታንና ምሕረትን ስለሰጠን፥ ልቦናቸውንም ኹልጊዜ ስለሚያራራልን አመስግኑ! የእኛንም ኃጢአታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* በክርስቶስ አምነው፡ ከዚህ በፊት ስላረፉት ኹሉ አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ዕረፍተ ነፍስን ስለሰጣቸው። የእኛንም ኃጢአታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* የክርስቲያን እምነት ስለደረሳቸውና ስለተፈጸመላቸው ወገኖች ኹሉ አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ለዚያ ሃይማኖት ስላበቃቸው፤ ተቀብለውም ስለባረካቸው፤ እስከመጨረሻዪቱ ሕቅታም ድረስ በቀናች ሃይማኖት ስላጸናቸው። የእኛንም ኃጢአታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* የእግዚአብሔር መንግሥት ስለኾነችው፡ ስለመላዋ ዓለም አገራችን ኢትዮጵያ፥ ስለቤተ ሕዝቧ፥ ስለቤተ ምልክናዋና ስለቤተ ክህነቷ፥ በእነዚህ አብያቷ መናብርት ላይ ስለተቀመጡትም ሥዩማኗ፥ ስለአገልጋዮቿም ኹሉ አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ የተቋሞቿን ህልውና ስላጸና፤ የአገልጋዮቿንም ሕይወት ስለሚጠብቅ፤ ሥዩማኑንም፡ ለኃላፊነታቸው ስለሚያበቃ። የእኛንም ኃጢአታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ኢየሱስ መሲሕ፡ በቀደሙት ሰዎች ልቦና ስለመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ስላጸናትና በሓዋርያት ጉባኤ ስለፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት ስለሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች ስለሚሰጡባት፡ ስለአንዲት ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፥ ስለአገልጋዮቿና ስለሕዝቡም ኹሉ መዳን፥ ስለቦታውም ኹሉ መጠበቅ አመስግኑ! የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ስለአንድነታችንና ስለዓለሙ ኹሉ አንድነት አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ኹላችንንም፡ በያለንበት ጠብቆ፡ በሰላም፡ ወደቅዱሱ ኪዳን የሕይወት ፍጻሜ ስላደረሰን። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ለከበረች ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መባን (እጅ መንሻን) ስላቀረቡ ሰዎች አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ባርኮ ስለተቀበለላቸው። በሥራቸውም እንዲጸኑ ስለረዳቸው። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ምእመናንና ምእመናትን፡ በየሥፍራቸው ኹሉ፡ በቸርነት ስለሚያስቡና ለበጎ ነገር ስለሚደክሙ፡ የቀና ሃይማኖት ስላላቸው ሰዎች አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ አሳባቸውንና ድካማቸውን ባርኮ፡ ዋጋቸውን ስለሰጣቸው። ይቅርታውንም ስላደረገላቸው። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ለቍርባን የሚኾን፡ ስንዴውን፥ ዕጣኑን፥ ዘቢቡን፥ የሚነበብባቸውን መጻሕፍት፥ ሌላውንም፡ ለቤተ መቅደስ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች አስበው በመስጠት ስለሚያገለግሉ ሰዎች አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ በመንግሥተ ሰማያት፡ የበለጠውን ዋጋ ስለሚሰጣቸው። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ስማቸውን፡ በእያንዳንዳቸው እንድንጠራ ስለሚያስፈልገን፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ዘርፍ፡ ለአገልግሎት ስለመረጥናቸው ተጠሪዎቻችን ኹሉ አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ጸጋውን፥ ኃይሉንና ሞገሱን አጎናጽፎ፡ በዓለሙ ባለሥልጣኖችና ሹማምንት ፊት፥ በፈራጆችም አደባባይ፡ ፍቅርን፥ መወደድን፥ መከበርን ስላደላቸው። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* በደዌ ሥጋ፥ በደዌ ነፍስ ለደከሙና ለተቸገሩ፥ ባል/ሚስት ለሌላቸውና ወላጆቻቸውን ላጡ፥ ለድኆችና ለተጨነቁ ሰዎች፥ ዘር ለዘሩ፥ እርሻ ላረሱ ገበሬዎች፥ ለሚሸጡ፥ ለሚገዙ ነጋዴዎች፥ በማናቸውም ቦታ፡ ጭንቀቷና ሥጋቷ ለተወገደላት ሰውነት ኹሉ አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ራርቶ፡ ይቅር ስላላቸውና የቸርነቱን ሥራ ስላደረገላቸው። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* በእሥር፥ በግዞትና በምርኮኝነት ተይዘው ለተጨነቁ፥ አገር ለቅቀው ለተሰደዱ፥ በአጋንንት አሽክላም ለተያዙ ሰዎች አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ ከእሥርና ከግዞት፥ ከምርኮኝነትና ከስደት፥ ከአጋንንት ቍራኝነትም ስላወጣቸው። ይቅርታውንም ሰጥቶ፡ እነርሱንም፥ እኛንም ስላዳነን። ኃጢኣታችንንም ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ለነፍሳቸው፡ ይቅርታን እየፈለጉ፡ ቅዱስ በኾነው በዚህ ጸሎት፡ በየሥፍራው ስለተሰበሰቡት ኹሉ አመስግኑ! ፈጣሪያችንና አምላካችን እግዚአብሔር፡ ይቅርታውን ፈጥኖ ስላደረገላቸው። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* በዚህ ዓመት፡ ስለዝናም መዝነብ፥ ስለባሕርና ስለወንዞችም መምላት አመስግኑ! እውነተኛው አምላካችን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በረከቱን ሰጥቶ፡ እስከልካቸው ስለመላቸው። ለምድርም፡ ልምላሜዋን አጎናጽፎ፡ ደስ ስላሰኛት። ሥጋዊዉን፡ ደማዊዉን ፍጡር ኹሉ በረድኤት ስላጸና። ለእንስሳትም ኹሉ ደኅንነትን ስለሰጠ። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* በጸሎታችን እናስባቸው ዘንድ፡ "አስቡን! አትርሱን!" ስላሉን ሰዎች አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ በበጎ ስላሰባቸው። በየጊዜውም ይቅር ስላላቸው። የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ይህችን ሳምንት፡ እግዚአብሔር፡ በበጎ ስለሚፈጽምልን፥ ከእኛም፡ የጠላትን መፈታተን አርቆ፡ ሰውነታችንን ከውድቀት ስለሚያድንልን፥ ይቅርም ስለሚለን አመስግኑ! የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ! (አቤቱ፡ ይቅር አልከን!)

*የጸሎቱ መሪ፡-* ጌታችንና አምላካችን እግዚአብሔር፡ ራርቶ፡ ይቅር ስላለን፥ ልመናችንንም ተቀብሎ፡ ለዚያ፡ ለፋሲካው ስለሚያበቃን፥ የትንሣኤውንም ብርሃን፡ በፍጹም ደስታ ስለሚያሳየን አመስግኑ! የእኛንም ኃጢኣታችንን ስላስተሰረየልን።

ሕዝቡ፡- እግዚኦ ተሣሃልከነ!

*ከዚህ ቀጥሎ፡ የጸሎቱ መሪና ሕዝቡ፡ ይህን ጸሎት፡ በዜማ እየተቀባበሉ ይስገዱ!*

ክርስቶስ አምላክነ፥ ዘመጽአ ወሐመ በእንቲአነ፥ በሕማማቲሁ ቤዘወነ!

ንሰብሖ፥ ወናልዕል ስሞ ኅቡረ፥ እስመ ውእቱ ገብረ መድኃኒተ፡ በብዝኀ ሣህሉ ወምሕረቱ!

ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን!

ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! እብኖዲ ናይናን፥ ኪርያላይሶን!
ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ታኦስ ናይናን፥ ኪርያላይሶን!
ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ማስያስ ናይናን፥ ኪርያላይሶን!
ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ኢየሱስ ናይናን፥ ኪርያላይሶን!
ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ክርስቶስ ናይናን፥ ኪርያላይሶን!
ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! አማኑኤል ናይናን፥ ኪርያላይሶን!
ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ትስቡጣ ናይናን፥ ኪርያላይሶን!

ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን! ኪርያላይሶን!

**ትርጉሙ**

ስለእኛ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፥ መከራን ተቀብሎ፥ ቤዛ ኾኖን ያዳነንን፡ ክርስቶስ አምላካችንን፡ እናመስግነው! ስሙንም፡ በአንድነት፡ ከፍ ከፍ እናድርግ! በብዙ ቸርነቱና ምሕረቱ፡ መድኃኒትነቱንና ሰላምነቱን አድርጎልናልና።

"ኪርያላይሶን! ናይናን!" የግሪክ ቃላት ሲኾኑ፡ በግእዝ፡ "እግዚኦ መሐርከነ!"፥ በኢትዮጵያኛ፡ "አቤቱ፥ ይቅር አልከን!" ማለት ነው።

"እብኖዲ፥ ታኦስ፥ ማስያስ፥ አማኑኤል፥ ትስቡጣ" የአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክነት መጠሪያዎቹ ናቸው።

*ኹሉም፡ አንገታቸውን ዝቅ በማድረግ፡-*

"እርሱን እናመልከው ዘንድ፡ እኛን ለፈጠረ እግዚአብሔር፡ ምስጋና ይገባል።

"አምላክን ለወለደች፡ ለንግሥታችንና እናታችን፡ ድንግል ማርያም ምስጋና ይገባል።

"ኃይልና ጋሻ፥ መድኃኒትም ለኾነን፡ ለክርስቶስ፡ በእንጨት ላይ ለመሰቀሉ፡ ምስጋና ይገባል።" *የሚል ትርጉም ያለውን ይህን የምስጋና ቃል፡ በኅብረት ዜማ ያሰሙ!*

ስብሓት ለእግዚአብሔር፡ ኪያነ ዘፈጠረ፡ ከመ ናምልኮ!
ስብሓት ለማርያም፡ እመ አምላክ፡ ንግሥትነ፤ ወመድኃኒትነ!
ስብሓት ለመስቀለ ክርስቶስ፡ ዕፀ ሰላምነ፤ ኃይልነ፤ ወጸወንነ!

*በስግደቱና በሰዓቱ ጸሎት ማብቂያ ላይ፡ ሕዝቡ፡ የ"*አቡነ ዘበሰማያት*"ን ጸሎት፡ በለሆሳስ* (በቀስታ) *እየደገሙ ይቀመጡ፤ የጸሎቱ መሪ ግን፡ ቆሞ፡ ፊቱን ወደሕዝቡ መልሶ፡ እንዲህ የሚለውን የቡራኬ ጸሎት ያሰማ፦*

የኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበር አንድነት የምትኾኑ፡ ወንድሞቼና እኅቶቼ ሆይ!

በዚህ መሰብሰባችን፡ አይሁድ፡ ፋሲካቸውን ባደረጉበት በዕለተ ዓርብ፡ በቅንዓታቸው፡ ለኃጥኣን አሳልፈው በሰጡት ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ የተቀበላቸውን መከራዎች፥ ሞቱን፥ ጎኑን መወጋቱን፥ ደሙን ማፍሰሱን እያሰብን ነው:: ስለዚህም፡ እግዚአብሔር፡ ድካማችንንና ጸሎታችንን፥ ስግደታችንንና መዝሙራችንን ተቀብሎልናል። ከሕሊና ሥጋ የተነሣ፡ በሕሊና መንፈስ የምንሻውን ኹሉ፡ በፈቃዱ ፈጽሞልናል። ተስፋ ትንሣኤውን ሰጥቶናል። የደስታውንም ቃል አሰምቶናል። በይቅርታውና በቸርነቱ፡ ከመከራ ሠውሮናል። ደቀ መዛሙርቱን እንደጎበኛቸው፡ እኛንም፡ እንደነርሱ ጎብኝቶናል። በኃጢኣት እንዳንወድቅ፡ ደግፎናል።! ከኃዘናችንም፡ አረጋግቶናል። ከድካማችንም አጽንቶናል።

ጌታችን፡ ኢየሱስ መሲሕ በሚመጣበት ጊዜ፡ በደስታው ቀን፡ ከእኛ ጋር፥ እናንተን ለማገልገል የተዘጋጀሁ ከምኾን፡ ከእኔ ከወንድማችሁ/ከእኅታችሁ ጋር፥ በሩቅና በቅርብ ካሉ፡ በጸሎታችን ከተማጸኑ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ኹሉ ጋር፡ ኹላችንንም አንድ አድርጎ፡ በሰማዩ አባታችን ጉባኤ፡ በቀኙ ያቁመን! ዘለዓለማዊው ተድላ ደስታ ወደሚገኝበት ቤቱ፡ ወደመንግሥተ ሰማያት ያግባን! ለዘለዓለሙ፤ አሜን::

*ከዚህ ቀጥሎ፡ አሰምቶ፡* "**እያንዳንዳችን፡ በለሆሳስ፡ ፵፩ ጊዜ፡ 'ኪራላይሶን!' እንበል!**" *ይበል!*

*በዚህ ጊዜ፡ ሕዝቡ ኹሉ ቆመው፡ በጣት አንጓ ቍጻሮ፡ ይህንኑ፡* " **'እግዚኦ መሐርከነ!**" *ወይም፡* "**አቤቱ፡ ይቅር አልከን!**" *የሚል ትርጕም ያለውን የንስሓ ጸሎት፡ በየራሳቸው የእስትንፋስ ድምፅ ይበሉ!*

*ወዲያው፡ ከዚህ አያይዞ፡* "**እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይኹን! የሚቀጥለውን ጸሎት ለማድረስ፡ ዛሬ (ወይም፡ ነገ)፡ ከሌሊቱ፥ ወይም፡ ከመዓልቱ፡ በ ___ ሰዓት እስክትመለሱ ድረስ፡ አኹን፡ በሰላም፡ ወደየበአታችሁ ኺዱ!**" *ለማለት፡* "**እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌክሙ! ሑሩ በሰላም! ወንዑ፥ ወተጋብኡ፡ በጊዜ ___ ሰዓት፡ ዘሰኑይ፥ ዘሠሉስ፥ ዘረቡዕ፥ ዘሓሙስ፥ ዘዓርብ፡ በሌሊት (አው፡ በመዓልት)**" *ብሎ በማወጅ፡ ሕዝቡን ያሰናብት!*

*የዕለቱ ሥርዓተ ጸሎት በሚያበቃበት፡ በመጨረሻው የሌሊቱ፥ ወይም፡ የመዓልቱ ክፍለ ጊዜ ማብቂያ ላይ ግን፡ በዚህ፡ በላይኛው የማሰናበቻ ቡራኬ ፋንታ፡ ይህንና የማሰናበቻውን አዋጅ ያሰማ!*

እነሆ! የዓለሙን ኹሉ ኀጢኣት የሚያስወግድ፡ የእግዚአብሔር በግ፡ ስለእኛ፡ መከራን ተቀበለ፤ ከኃጢኣት ቀንበር፡ ነጻ አወጣን፤ ከሰይጣንም እጅ፡ በክቡር ደሙ፥ መድኃኒትና ሰላማችን በኾነ መስቀሉም አዳነን፡፡

አቤቱ! ድካማችንን፥ ጸሎታችንንም፡ ተቀበልህ! የጠላታችንን የዲያብሎስን ኃይል፡ ከእግራችን በታች ጣልኸው! የሚያጠምድበትን ወጥመዱንም፡ አራቅህልን!

ይህችን ሰሞን፡ በሰላምና በፍቅር አንድነት፡ በደኅና እንደምታስፈጽመን፥ ቅድስት የኾነች፡ የትንሣኤህንም ብርሃን፡ በፍጹም ተድላ ደስታ እንደምታሳየን፡ በእመቤታችንና በንግሥታችን፡ በቅድስት ድንግል ማርያም እናትነት፥ በጻድቃንና በሰማዕታትም በረከት እናምናለን፤ አሜን፡፡

*እስከዚህ ያለው ሥርዓተ ጸሎት፡ ከሰኞ እስከ ሓሙስ፡ ከቀትር በኋላ ፱ ሰዓት ድረስ ያለው ሲኾን፡ የሓሙሱ "ኅጽበተ እግር" የሚባለው፡ የእግር አጠባ ሥርዓት፡ ከዚህ እንደሚከተለው ይፈጸማል፡-*

*የዕለቱ ምንባብ፡ እስከቀትር በኋላ ፱ ሰዓት ድረስ ያለው እንደተጠናቀቀ፡ አንዱ፡ ለእጅ የሚኾን፥ ሌላው፡ የወይን ሓረግ ቅጠል የተዘፈዘፈበት ኾኖ፡ ለእግር የሚኾን፡ ንጹሕ ውኃ፡ እስከእኩሌታቸው የመላባቸው፡ ኹለት የመታጠቢያ ሣህኖች፡ ከማበሻ ጋር፡ በጠረጴዛ ላይ ይቅረቡ!*

*በዚያ ላይ፡ የቡራኬውና የወንጌሉ ሥርዓተ ጸሎት፡ በጸሎቱ መሪ ይፈጸም! የኅጽበተ እግሩ ሥርዓት በሚካኼድበት ጊዜ፡ የጸሎቱ ተሳታፊዎች፡ እንዲህ የሚለውን የግእዝ መዝሙር፡ እጥበቱ እስኪያበቃ ድረስ፡ በኅብረትና ባለማቋረጥ ይዘምሩ!*

**ሓዋርያቲሁ ከበበ፤ እግረ አርዳኢሁ ኀፀበ፤ ኮኖሙ አበ ወእመ፤ ወመህሮሙ ጥበበ፤ ሃሌ ሉያ፡፡**

**ትርጉሙ፡**

ሓዋርያቱን በዙርያው ሰበሰበ፤ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ፤ ለእነርሱ፡ አባትም፥ እናትም ኾናቸው፤ ጥበብንም አስተማራቸው፤ ከዓለም አስቀድሞ የነበረው፥ ዓለሙንም አሳልፎ የሚኖረው፡ እርሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ!

*ከዚህ አስቀድሞ፥ ከዚህም በኋላ የሚባለው ምንባብና ምስባክ፡ በዕለቱ ድልድል ውስጥ ተመልክቶ ይገኛል፡፡*

## የዓርቡ የስቅለት ሥርዓት

*የዕለተ ዓርቡ የስቅለተ ክርስቶስ ሥርዓተ ጸሎት ምንባብ፡ እስከንጋቱ፡ ፲፩ ሰዓት ድረስ ያለውን ጨምሮ ካበቃ በኋላ፡ ከማለዳው፡ ፩ ሰዓት ጀምሮ፡ በዚህ ዕለት የሚጸለየውና የሚዘመረው ኹሉ፡ ከሰኞ እስከሓሙስ ከሰነበተው ከግእዙ ተለይቶ፡* ***<u>በዕዝል የዜማ ስልት</u>*** *ይኾናል፡፡*

*ይኸው፡ የማለዳው፡ ፩ ሰዓት ምንባብ ከመጀመሩ በፊት፡ ካህናቱና ሕዝቡ፡ የዓለሙን መድኃኒት፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሕማማተ መስቀል በማሰብ፡ ቆመው፡ የተለመደውን የመክፈቻ ጸሎት እንደጨረሱ፡* ከ"ለከ ኃይሉ" *መዝሙር አስቀድመው፡ በተለይ፡ ለዚህ ዕለትና መዓልት ከተመደቡት፡ የየጊዜያቱ ጸሎታት፡ የሃሌታ ዜማዎች መካከል፡ ለዚህ ሥርዓት የተመረጠውን፡ ከዚህ የሚከተለውን የመግቢያ ዜማ፡ በዕዝል ስልት ይበሉ!*

**<u>የማለዳው ፩ ሰዓት</u>**

**ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ!**
**ተሰቅለ ተሰቅለ ተሰቅለ ተሰቅለ! ወሓመ! ቤዛ ኵሉ ኮነ! ዬ! ዬ! ዬ!**
**በመስቀሉ ቤዘወነ! እሞት ወባልሃነ!**

**<u>ትርጕሙ፡-</u>** ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ የነበረውና ዓለምን አሳልፎ የሚኖረው ፈጣሪ አምላክ፡ ወዮ! ወዮ! ወዮ! ስለእኛ ሰው ኾኖ፡ መከራን ተቀበለ! ተሠቃየ! ተሰቀለ! ሞተ! በጦር ተወጋ! ተቀበረ! ስለዓለሙ ኹሉ መሥዋዕት ኾነ! እንዲህ ኾኖ በመስቀሉ፡ ከዲያብሎስ የባርነት ግዛት፡ ነጻ አወጣን! ከኃጢኣት ቀንበር አላቀቀን! ከሞት ፍዳም ተቤዠን!

*ከዚህ አያይዘው፡* የ"ለከ ኃይሉ"ን *የስግደት ጸሎት፡ በዚያው በዕዝሉ ዜማ ይበሉት!*

*ለሰዓቱ የተመደበው ምንባብ ካበቃ በኋላ፡* **"የዓመፅ ምስክሮች ተነሡብኝ! የማላውቀውንም፡ በእኔ ላይ ተናገሩ!"** *የሚል ትርጉም ያለው፡ እንዲህ የሚለው ምስባክ፡ በዲያቆኑ/በዲያቆኒቱ፡ ዘለግ ባለ የኀዘን ዜማ፡ ይዘመር!*

**ተንሥኡ ላዕሌየ ሰማዕተ ዐመፃ፤**
**ወዘኢየአምር ነበቡ ላዕሌየ፤**
**ተንሥኡ ላዕሌየ ሰማዕተ ዐመፃ፤**

*ሕዝቡ፡ ይህንኑ፡ እየሰገዱና እየተቀበሉ፡ ሦስት ጊዜ መላልሰው ይዘምሩት!*

**"የቅዱስ ወንጌልን ቃል ለመስማት የተዘጋጀን ኾነን እንገኝ ዘንድ፡ ተነሥታችሁ ቁሙና አዳምጡ!"** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው መመሪያ፡ በዲያቆኑ/በዲያቆኒቱ የኀዘን ዜማ ይዘመር!*

**ቁሙ ወአጽምኡ! ከመ ንኩን ድልዋነ ለሰሚአ ወንጌል ቅዱስ፡፡**

*ሕዝቡ፡ እየሰገዱ፡* **"ጌታችንና አምላካችን! ማርከን! ይቅርም አልኸን! ለእግዚአብሔር መንግሥትም፡ የበቃን አደረግኸን!"** *የሚል ትርጉም ያለውንና እንዲህ የሚለውን መልስ፡ በኀዘን ዜማ ይስጡ!*

**እግዚእነ፥ ወአምላክነ!**
**መሓርከነ ፤ ወተሣሃልከነ፤ ወረሰይከነ ድልዋነ፡ ለመንግሥተ ሰማያት።**

**"ማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስና ዮሓንስ፡ ያወጁትን፡ ቅዱሱን የእግዚአብሔርን የምሥራች ቃል፡ እነሆ ላሰማችሁ!"** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው መልእክት፡ በካህኑ/በካህኒቱ፡ ልዑል የኀዘን ዜማ ይተላለፍ!*

**ወንጌል ቅዱስ፡ ዘዜነዉ፡ ማቴዎስ፥ ወማርቆስ፥ ሉቃስ፥ ወዮሓንስ፡**
**ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።**

*ሕዝቡ፡ እየሰገዱ፡* **"ጌታችንና አምላካችን ክርስቶስ ሆይ! ኹልጊዜም፡ ለአንተ፡ ምስጋና ይገባሃል!"** የሚል ትርጉም ያለውንና እንዲህ የሚለውን ምላሽ፡ በኀዘን ዜማ ይስጡ!

**ስብሓት ለከ ክርስቶስ፥ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ኵሎ ጊዜ!**

**"የማይሞት ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ! አቤቱ ይቅር አልኸን! የማይሞት! ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፥ በዮርዳኖስ የተጠመቀ! በዕፀ መስቀል ላይ የተሰቀለ! አቤቱ ይቅር አልኸን!"** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው የኪዳን ጸሎት፡ ለእያንዳንዱ የወንጌሉ ምንባብ፡ መግቢያ ተደርጎ፡ በኀዘን የንባብ ድምፅ፡ በካህኑ/በካህኒቱ ይሰማ!*

**ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፥ ዘኢይመውት! ዘተወልደ እማርያም፥ እምቅድስት ድንግል! ተሣሃልከነ እግዚኦ! ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፥ ዘኢይመውት! ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ! ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል፥ ተሣሃልከነ እግዚኦ!**

*በመጀመሪያ፡ የማቴዎስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **"የካህናት አለቆች፡ ኢየሱስን፡ አሥረው ይዘው፥ ሌሊቱን ሙሉ፡ ሲመክሩበት ካደሩ በኋላ፡ ሲነጋ፡ በወንጀለኛ እንጨት መስቀል ላይ ሊሰቅሉት ተስማምሙ!"** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ወጸቢሖ፡ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት፡ ይስቅልዎ ለኢየሱስ ዲበ ዕፀ መስቀል ዘእቡስ።**

*ቀጥሎ፡ የማርቆስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* “**የካህናት አለቆች፡ ኢየሱስን፡ አሥረው ይዘው፥ ሌሊቱን ሙሉ፡ ሲመክሩበት ካደሩ በኋላ፡ ሲነጋ፡ ወደፍርድ አደባባይ አወጡት!**” *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ወጸቢሖ፡ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት፡ አውጽእዎ ለኢየሱስ፡ ውስተ ዐውደ ምኵናን፡፡**

*ከዚያ፡ የሉቃስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* “**የካህናት አለቆች፡ ኢየሱስን፡ አሥረው ይዘው፥ ሌሊቱን ሙሉ፡ ሲመክሩበት ካደሩ በኋላ፡ ሲነጋ፡ የፊጥኝ ዐሥረው፡ ለጲላጦስ፡ አሳልፈው ሰጡት!**” *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ወጸቢሖ፡ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት፡ ሓመይዎ ለኢየሱስ፥ ወመጠውዎ ለጲላጦስ፡፡**

*በመጨረሻ፡ የዮሓንስን የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* “**የካህናት አለቆች፡ ኢየሱስን፡ አሥረው ይዘው፥ ሌሊቱን ሙሉ፡ ሲመክሩበት ካደሩ በኋላ፡ ሲነጋ፡ በዚያን ጊዜ፡ የፍርዱ ችሎት ወደተዘጋጀበት አደባባይ አመጡት!**” *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ወጸቢሖ፡ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት፡ አውጽእዎ አፍኣ ለኢየሱስ፥ ወነበረ ዓውዶ ሶቤሃ፡፡**

*እዚህ ላይ፡* “**ጽንዓ ዛቲ**” *የሚለው፡ ምስጋናና ተከታታዩ ስግደት ተካኼዶ፡ የሰዓቱ ሥርዓተ ጸሎት ይከናወናል፡፡*

## <u>የጧቱ፡ ፫ ሰዓት፤</u>

*ጸሎቱ፡ ከላይ በ፩ኛው ሰዓተ ጊዜ፡ የተካኼደውን ሥርዓትና ተራ የሚከተል ኾኖ፡ የመልእክቶቹ ፍሬ ነገር ግን፡ ከዚህ የሚቀጥለውን ይዞ ይቀርባል፡-*

“**አቤቱ! የሚያጠቁኝን፡ ተከላከልልኝ! የሚዋጉኝንም፡ ተዋጋልኝ!**” *የሚል ትርጉም ያለው፡ የመዝሙር ፴፬፡ የመግቢያ ቃላት፡ በዲያቆኑ/በዲያቆኒቱ፡ ዘለግ ባለ የኀዘን ዜማ፡ ይሰማ!*

**ግፍዖሙ እግዚኦ፡ ለእለ ይገፍዑኒ!**
**ጽብኦሙ እግዚኦ፡ ለእለ ይጸብኡኒ**
**ግፍዖሙ እግዚኦ፡ ለእለ ይገፍዑኒ!**

*ሕዝቡ፡ ይህንኑ ቃል፡ እየሰገዱ፡ ተቀብለው ይዘምሩት!*

*መዝሙሩ፡ በዲያቆኑ/በዲያቆኒቱ የኀዘን ውርድ ንባብ፡ እሰባት ቦታዎች ላይ እየታረፈ፡ ከመጀመሪያው አንሥቶ ይሰማ!*

*ንባቡ ባረፈ ቍጥር፡ ይህንኑ፡* **“ግፍዖሙ እግዚኦ፡ ለእለ ይገፍዑኒ!”** *የሚለውን የአቤቱታ ቃል፡ በዚያው ዜማ፡ በካህኑ/በካህኒቱ ይዜም!*

*ሕዝቡ፡ ይህንኑ ቃል፡ እየሰገዱና እየተቀበሉ፡ አንዳንድ ጊዜ ይዘምሩት!*

**“ብዙ ውሾች ከበቡኝ! ክፉዎችም፡ በየማኅበሮቻቸው ተደራጅተው ያዙኝ!”** *የሚል ትርጉም ያለው፡ እንዲህ የሚለው ምስባክ፡ በዲያቆኑ/በዲያቆኒቱ፡ ዘለግ ባለ የኀዘን ዜማ፡ ይዘመር!*

**ዐገቱኒ ከለባት ብዙኃን፤**
**ወአኀዙኒ ማኅበሮሙ ለእኩያን**
**ዐገቱኒ ከለባት ብዙኃን፤**

*ሕዝቡ፡ ይህንኑ፡ እየሰገዱና እየተቀበሉ፡ ሦስት ጊዜ መላልሰው ይዘምሩት!*

*የወንጌሉ ምንባብ ጸሎት፡ ከላይ፡ በ፩ኛው ሰዓት በቀረበው መልክ በሚካኼድበት ጊዜ፡ በመጀመሪያ፡ የማቴዎስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **“ጊዜው፡ ጧት ፫ ሰዓት ሲኾን፡ ኢየሱስን ይዘው፡ ሊሰቅሉት ወሰዱት፤”** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት፡ አኀዝዎ ለኢየሱስ፡ ወወሰድዎ ይስቅልዎ።**

*ቀጥሎ፡ የማርቆስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **“ጲላጦስ፡ ኢየሱስን ካስገረፈው በኋላ፡ ጊዜው፡ ጧት ፫ ሰዓት ሲኾን፡ ሊሰቅሉት ወሰዱት፤”** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት፡ ቀሠፎ ጲላጦስ፡ ለኢየሱስ፡ ወወሰድዎ ይስቅልዎ።**

*ከዚያ፡ የሉቃስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **“ጊዜው፡ ጧት ፫ ሰዓት ሲኾን፡ በርባንን አድኖላቸው፡ ኢየሱስን ግን፡ ይሰቅሉት ዘንድ ሰጣቸው፤”** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት፡ አሕየወ ሎሙ በርባንሃ፡ ወወሀቦሙ ኢየሱስሃ ይስቅሉ።**

*በመጨረሻ፡ የዮሓንስን የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **“ጊዜው፡ ጧት ፫ ሰዓት ሲኾን፡ ኢየሱስን፡ ወደፍርድ አደባባይ አወጡት!”** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት፡ ወሰድዎ ለኢየሱስ፡ ውስተ ዐውደ ምኵናን።**

*እዚህ ላይ፡ “ጽንዓ ዛቲ” የሚለው፡ ምስጋናና ተከታታዩ ስግደት ተካኼዶ፡ የሰዓቱ ሥርዓት ጸሎት ይከናወናል።*

## <u>የቀትሩ፡ ፮ ሰዓት፤</u>

*ጸሎቱ፡ ከላይ በ፩ኛው ሰዓተ ጊዜ፡ የተካኼደውን ሥርዓትና ተራ የሚከተል ኾኖ፡ የመልእክቶቹ ፍሬ ነገር ግን፡ ከዚህ የሚቀጥለውን ይዞ ይቀርባል፡-*

**"አቤቱ! አምላካችን! ሊቃችን! ለእኛ፡ ቤዛ ኾነህ፡ ቅዱስ ደምህን ላፈሰስህበት መስቀልህና ለቅድስቲቱ ትንሣኤህ እየሰገድን፡ ኹላችን እናመሰግንሃለን!"** *የሚል ትርጉም ያለው፡ እንዲህ የሚለው፡ የምስክርነትና የምስጋና ቃል፡ ዘለግ ባለ፡ የካህኑ/የካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይሰማ!*

**ለመስቀልከ ንሰግድ ኦ ሊቅነ፤**
**ወለትንሣኤከ ቅድስት፡ ንሰብሕ ኵልነ፤**
**ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፡፡**

*ሕዝቡ፡ ይህንኑ፡ እየሰገዱ፡ ተቀብለው፡ ሦስት ጊዜ ይዘምሩት!*

*ከዚህ ቀጥሎ፡* **"እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፤ አጥንቶቼንም ኹሉ ቈጠሩ፡፡"** *የሚል ትርጉም ያለው፡ እንዲህ የሚለው፡ የምስባኩ መዝሙር፡ ዘለግ ባለ፡ በዲያቆኑ/በዲያቆኒቱ፡ የኀዘን ዜማ፡ ይዘመር!*

**ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ፤**
**ወኈለቊ ኵሉ አዕፅምትየ፤**
**ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ፤**

*ሕዝቡ፡ ይህንኑ፡ እየሰገዱና እየተቀበሉ፡ ሦስት ጊዜ መላልሰው ይዘምሩት!*

*የወንጌሉ ምንባብ ጸሎት፡ ከላይ፡ በ፩ኛው ሰዓት በቀረበው መልክ በሚካኼድበት ጊዜ፡ በመጀመሪያ፡ የማቴዎስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **"ጊዜው፡ ፮ ሰዓት ሲኾን፡ ኢየሱስን፡ ልብሱን አልብሰው፥ መስቀሉን አሸክመው፡ ሊሰቅሉት ወሰዱት፤"** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ስድስቱ ሰዓት፡ አልበስዎ አልባሲሁ፡ ለኢየሱስ፡ ወወሰድዎ ይስቅልዎ፡፡**

*ቀጥሎ፡ የማርቆስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **"ጊዜው፡ ፮ ሰዓት ሲኾን፡ ሊሰቅሉት ሲወስዱት፡ ስለደከመባቸው፡ ስምዖን የተባለውን መንገደኛ፡ መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት፤"** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ስድስቱ ሰዓት፡ አበጥዎ ለስምዖን፡ ከመ ይጹር መስቀሎ፡፡**

*ከዚያ፡ የሉቃስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* “ጊዜው፡ ፮ ሰዓት ሲኾን፡ ኢየሱስን፡ 'ቀራንዮ' በተባለው ሥፍራ ሰቅሉት!” *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ስድስቱ ሰዓት፡ ሰቀልዎ ለኢየሱስ፡ በቀራንዮ መካን፡፡**

*በመጨረሻ፡ የዮሓንስን የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* “ጊዜው፡ ፮ ሰዓት ሲኾን፡ ሊቃነ ካህናቱ፡ ቀትር ሣለ፡ ኢየሱስን፡ በኹለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉት!” *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ስድስቱ ሰዓት፡ ቀትር ሶቤሃ፡ ሊቃነ ካህናት፡ ሰቀልዎ ለኢየሱስ፡ ማዕከለ ክልኤ ፈያት፡፡**

*ይህ ምንባብና ጸሎት እንዳበቃ፡ ካህናቱ፡ እመሬት ላይ ተቀምጠው፥ ራሳቸውን ሸፍነውና አንገታቸውን እየጕልበታቸው ላይ ደፍተው፡* “አቤቱ፡ በመንግሥትህ በተገለጥህ ጊዜ አስበን!” *የሚል ትርጉም ያለውንና እንዲህ የሚለውን የግሪክኛ ቃለ ጸሎት፡ ፫ ጊዜ፡ በኀዘን ዜማ ያሰሙ!*

**አምንስቲቲ፡ ሙኪርያ፡ ኣንቲ ፋሲልያሱ!**
**አምንስቲቲ፡ ሙዓግያ፡ ኣንቲ ፋሲልያሱ!**
**አምንስቲቲ፡ ሙዳሱጣ፡ ኣንቲ ፋሲልያሱ!**

*ሕዝቡም፡ ከካህናቱ ጋር ዐብረው፡ የዚሁ፡ የግሪክኛው ጸሎት፡ ተመሳሳይ የኾነውን ግእዙን፡ እንዲህ እያሉ፡ ቆመውና እየሰገዱ ያዚሙት!*

**ተዘከርከነ እግዚኦ፡ በውስተ መንግሥትከ፤**
**ተዘከርከነ እግዚኦ፡ ኦ ሊቅነ፤**
**ተዘከርከነ እግዚኦ፡ በውስተ መንግሥትከ፤**

*በመጨረሻ፡ ኹሉም በኅብረት፡* “አቤቱ፡ በቅዱስ መስቀልህ ላይ ተሰቅለህ ሣለህ፡ በቀኝህ የተሰቀለውን ወንጀለኛ፡ በመንግሥትህ እንዳሰብኸው፡ እኛንም፡ አስበን !” *የሚል ትርጉም ያለውንና እንዲህ የሚለውን ማጠቃለያ ጸሎት ያዚሙት!*

**በከመ ተዘከርኮ፡ ለፈያታዊ ዘየማን፥ እንዘ ሀሎከ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ፡፡**

*እዚህ ላይ፡* “ጕንዓ ዛቲ” *የሚለው፡ ምስጋናና ተከታታዩ ስግደት ተካኼዶ፡ የሰዓቱ ሥርዓተ ጸሎት ይከናወናል፡፡*

<u>**የቀትሩ በኋላ ፱ ሰዓት፤**</u>

*ጸሎቱ፡ ከላይ በ፩ኛው ሰዓተ ጊዜ፡ የተካኼደውን ሥርዓትና ተራ የሚከተል ኾኖ፡ የመልእክቶቹ ፍሬ ነገር ግን፡ ከዚህ የሚቀጥለውን ይዞ ይቀርባል፡-*

**"የማይሞት መለኮት፡ ስለእኛ፡ የሞት ጽዋን ተቀብሎ፡ በሰውነቱ ሞተ! ወዮ ለዚህ አንክሮ ይገባል!"** *የሚል ትርጉም ያለውን፡ የተዘክሮ ቃል፡ ካህናቱ፡ በታላቅ የኀዘን ዜማ ድምፅ፡ እንዲህ እያሉ ያሰሙ!*

**አ! ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ!**
**አ! ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ!**
**አ! ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ!**

*ሕዝቡ፡ ይህንኑ፡ እየሰገዱ፡ ተቀብለው፡ ሦስት ጊዜ ይዘምሩት!*

*ከዚህ ቀጥሎ፡* **"ለመብሌ፡ ሓሞትን ሰጡኝ፤ ለጥማቴም፡ ሆምጣጤ አጠጡኝ፡፡"** *የሚል ትርጉም ያለው፡ የምስባክ መዝሙር፡ ዘለግ ባለ፡ በዲያቆኑ/በዲያቆኒቱ፡ የኀዘን ዜማ፡ ይዘመር!*

**ወወደዩ ሓሞተ ውስተ መብልዕየ፤**
**ወአስተዩኒ ብሒአ ለጽምእየ፤**
**ወወደዩ ሓሞተ ውስተ መብልዕየ፡፡**

*ሕዝቡ፡ ይህንኑ፡ እየሰገዱና እየተቀበሉ፡ ሦስት ጊዜ መላልሰው ይዘምሩት!*

*የወንጌሉ ምንባብ ጸሎት፡ ከላይ፡ በ፩ኛው ሰዓት በቀረበው መልክ በሚካኼድበት ጊዜ፡ በመጀመሪያ፡ የማቴዎስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **"ጊዜው፡ ፱ ሰዓት ሲኾን፡ ኢየሱስ፡ 'አምላኬ! አምላኬ!" ብሎ፡ በቃሉ ጮኾ ተጣራ፡፡"** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ተስዓቱ ሰዓት፡ ጸርሓ ኢየሱስ በቃሉ፡ ወይቤ፡ "ኤሎሄ! ኤሎሄ!"**

*ቀጥሎ፡ የማርቆስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **"ጊዜው፡ ፱ ሰዓት ሲኾን፡ ኢየሱስ፡ ድምፁን፡ በቃሉ፡ ጮኾ ካሰማ በኋላ፡ ነፍሱ፡ ከሥጋው ተለየች!"** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ተስዓቱ ሰዓት፡ ገዐረ ኢየሱስ፡ በቃሉ፡ ወወጽአት መንፈሱ ሶቤሃ፡፡**

*ከዚያ፡ የሉቃስ የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **“ጊዜው፡ ፱ ሰዓት ሲኾን፡ ኢየሱስ፡ በቃሉ ጮኸ! ነፍሱንም፡ ከሞት ኃይል ታድጎ፡ አደራ አስጥበቀ፤”** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ተስዓቱ ሰዓት፡ ከልሓ ኢየሱስ በቃሉ፡ ወአማሕፀነ ነፍሶ እሞት፡፡**

*በመጨረሻ፡ የዮሓንስን የወንጌል ንባብ ሲያበቃ፡* **“ጊዜው፡ ፱ ሰዓት ሲኾን፡ ኢየሱስ፡ ራሱን ዘንበል አድርጎ፡ 'ኹሉ ተፈጸመ!' አለ፡፡”** *የሚል ትርጉም ያለውና እንዲህ የሚለው ዝክረ ነገር፡ በካህኑ/በካህኒቱ የኀዘን ዜማ ይታወስ! ሕዝቡም ተቀብለው፡ እየሰገዱ ይዘምሩት!*

**ጊዜ ተስዓቱ ሰዓት፡ አጽነነ ርእሶ ኢየሱስ፡ ወይቤ፡ “ተፈጸመ ኵሉ!”**

*እዚህ ላይ፡* **“ጽንዓ ዛቲ”** *የሚለው፡ ልመናና ተከታታዩ ስግደት ተካኼዶ፡ የሰዓቱ ሥርዓተ ጸሎት ይከናወናል፡፡*

**የሥርዓተ ጾሙ፥ ጸሎቱና ስግደቱ ማጠቃለያ፤**

*ካህናቱ፡ ቀጥለው፡ ከሥርዓቱ ተካፋዮች መካከል፡ የግል ንስሓቸውን ለማድረስ፡ ወደእነርሱ የሚቀርቡትን ተነሳሕያን (ንስሓ ተቀባዮች)፡ የርግበ ኖኅ፡ የምሥራች ቀምበጥ ምሳሌ በኾነው፡ በወይራ ቅጠል ዝንጣፊ፡ ትከሻቸውን በመጠብጠብ፡ እንደየዓቅማቸው የንስሓ ስግደትን ይሰጧቸዋል፤ በዚህም፡ የስቅለተ ዓርቡ ሥርዓተ ጾም፥ ጸሎትና ስግደት ይፈጸማል፡፡*

*ይህ እንደተከናወነ፡ በካህናቱ መሪነት፡ በእንተ ማርያምን የያዘ፡ የ፲፪፥ ፲፪ ጊዜ እግዚኦታን ያድርሱ!*

*ከዚህ በኋላ፡ ካህናቱና ሕዝቡ፡* **“አምላካችንና መድኃኒታችን፥ ሊቀ ካህናችንና ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው ኾኖ በተቀበላቸው ፈተናዎችና መከራዎች፡ ዲያብሎስን ድል አደረገልን፤ ተሰቅሎ ባፈሰሰው ደሙ፡ ኃጢኣትን ደምሰሰልን፤ በመሞቱና በመቀበሩ፡ ሞትንና መቃብርን አጠፋልን፤”** *ሲሉ፡ እንዲህ እያሉ፡ እየዘመሩ ያሸበሽባሉ፡፡*

*ይህ የሚያሸበሽቡት ዝማሬ፡ ሙሴ፡ በእግዚአብሔር ተአምራዊ ኃይል፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ ከባርነት፥ ከመቅሠፍትና ከሞት፡ ነጻ አውጥቶ፡ ከግብፅ፡ ወደምድረ ከነዓን እየመራ፡ በሚጓዙበት ጊዜ፡ ከኤርትራ ባሕር ሲደርሱ፡ የፈርዖን ሠራዊት፡ ከኋላቸው መጥቶባቸው፡ ሣለ፡ ባሕሩ፡ ከኹለት ተከፍሎላቸው፡ በደኅና ስለተሻገሩ፡ ጠላቶቻቸው ግን፡ ሠጥመው ስላለቁ፡ በታላቅ ደስታ ኾነው፡ ለፈጣሪያቸው የዘመሩት ነው፡፡*

**“በፍጥረቱ ኹሉ የተመሰገነ፥ ምስጉን እግዚአብሔርን፡ እኛም እናመሰግነዋለን!”** *የሚል ትርጉም ያለው፡ ይኸው ዝማሬ፡ እንዲህ ይነበባል፦*

**ንሴብሖ፥ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር፤ ስቡሓ ዘተሰብሓ፥ ስቡሓ ዘተሰብሓ፡፡**

*ሽብሸባው፡ ባጭሩ እንዳበቃ፡ ካህናቱ፥ ወይም፡ የጸሎቱ መሪ፡ ሕዝቡን፡ በቡራኬ ጸሎት ያሰናብቱና፡ የዕለቱ ሥርዓት ፍጻሜ ይኾናል፡፡*

---

# <u>የምንባቦችና ምስባኮች ዝርዝር፡</u>

*ከቅዱሳት መጻሕፍት የተውጣጣው፡ የሰሙነ ሕማማት፡ የየዕለቱ ምንባቦችና ምስባኮች ዝርዝር፡ ከዚህ የሚከተለው ነው፡-*

## <u>የሰኞ</u>

### <u>፩ኛ፡ እሑድ÷ በምሽቱ፡ ፩ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ሶፎ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፩-፲፰፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፳፯÷ ቁ. ፯-፰፡፡

| | |
|---|---|
| እሴብሕ ወእዜምር ለእግዚአብሔር፤ | ለእግዚአብሔር፡ እቀኛለሁ፤ እዘምርለታለሁ፤ |
| ሰምዓኒ እግዚኦ ቃልየ ዘሰአልኩ ኀቤከ፤ | አቤቱ፡ ወደአንተ የጮኽሁትን ቃሌን ሰማህ! |
| ተሣሃልከኒ ወሰምዓከኒ፡ ለከ ይብለከ ልብየ፡፡ | ልቤ፡ "ማርኸኝ÷አደመጥኸኝም!" ይልሃል፡፡ |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፲፪÷ ቁ. ፳-፵፮፡፡

### <u>፪ኛ፡ እሑድ÷ በማታው፡ ፫ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ሶፎ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፲፬-፲፯፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፳፰÷ ቁ. ፮-፯፤ ፰-፱፡፡

| | |
|---|---|
| አድኅንከ ሕዝበከ÷ ወባረክከ ርስተከ፤ | ሕዝብህን አድን! ርስትህንም ባርክ! |
| ረዐይኮሙ ወአልዐልኮሙ እስከለዓለም፤ | ጠበቅሃቸው÷ እስከዘለዓለምም ከፍ አደረግሃቸው፤ |
| ይትባረክ እግዚአብሔር እስመ ሰምዓኒ ቃለ ስእለትየ፡፡ | እግዚአብሔር ይመስገን የልመናዬን ቃል ሰምቶኛልና፡፡ |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፱÷ ቁ. ፲፰-፳፪፡፡

### <u>፫ኛ፡ ሰኞ÷ በሌሊቱ፡ ፮ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ኢዩ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፭-፲፮፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፳፱÷ ቁ. ፩-፪፡፡

| | |
|---|---|
| አምጽኡ ለእግዚአብሔር ውሉደ አማልክት፤ | የአምላክ ልጆች! ለእግዚአብሔር አመጡ! |
| አምጽኡ ለእግዚአብሔር ዕጕለ ሓራጊት፤ | ለእግዚአብሔር፡ የበግ ጠቦት አመጡ! |
| አምጽኡ ለእግዚአብሔር ክብረ ወስብሓተ፡፡ | ክብርና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አመጡ! |

ወንጌል፡- ማር. ምዕ. ፲÷ ቁ. ፵፪-፵፬፡፡

<u>፩ኛ: ሰኞ÷ በነግሁ: ፱ ሰዓት፤</u>

ምንባብ:- ሚክ. ምዕ. ፯÷ ቁ. ፫-፲፩::

ምስባክ:- መዝ. ፲፮÷ ቁ. ፫-፬::

| | |
|---|---|
| ሓወጽከኒ ሌሊተ÷ ወፈተንኮ ለልብየ፤ | በሌሊት ጎበኘኸኝ÷ ልቤንም ፈተንኸው፤ |
| አመከርከኒ: ወኢተረክበ ዐመፃ በላዕሌየ፤ | ፈተንኸን፤ ዐመፃም አልተገኘብኝም፤ |
| ከመ ኢይንብብ አፉየ: ግብረ ዕጓለመሕያው፤ | የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር: ፈቃዴ ነው:: |

ወንጌል:- ማር. ምዕ. ፲፬÷ ቁ. ፶፫-፸፪::

<u>፪ኛ: ሰኞ÷ በንጋቱ: ፲፩ ሰዓት፤</u>

ምንባብ:- ሚክ. ምዕ. ፫÷ ቁ. ፩-፬::

ምስባክ:- መዝ. ፲፯÷ ቁ. ፵፰::

| | |
|---|---|
| ዘይባልሓኒ እምጸላእትየ ምንስዋን፤ | ከጠላቶቼ የሚታደገኝ: እርሱ ነው፤ |
| ወዘያሌዕለኒ እምእለ ቆሙ ላዕሌየ፤ | በእኔም ላይ ከቆሙ: ከፍ ከፍ የሚያደርገኝ፤ |
| እምብእሲ ገፋዒ ባልሓኒ:: | ከግፈኛ ሰው አዳነኝ:: |

ወንጌል:- ማቴ. ምዕ. ፳፮÷ ቁ. ፶፯-፸፭::

<u>፫ኛ: ሰኞ÷ በማለዳው: ፩ ሰዓት፤</u>

ምንባብ:- ዘፍጥ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፩-፴፩፤
ኢሳ. ምዕ. ፪÷ ቁ. ፩-፱፤
ሲራ. ምዕ. ፩::

ምስባክ:- መዝ. ፸፩÷ ቁ. ፲፰-፲፱::

| | |
|---|---|
| ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እሥራኤል፤ | የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፤ |
| ዘገብረ መንክረ ዐቢየ ባሕቲቱ፤ | ብቻውን: ታላላቅ ተአምራትን የሚያደርግ፤ |
| ወይትባረክ ስመ ስብሓቲሁ:: | የምስጋናው ስም ይባረክ! |

ወንጌል:- ማር. ምዕ. ፲፭÷ ቁ. ፲፫-፳፮::

## <u>፯ኛ፡ ሰኞ፥ በጧቱ፡ ፫ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ኢሳ. ምዕ. ፭፥ ቁ. ፳፩-፴፤
ኢዩ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፳፩-፴፪፤
ኢዩ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፳፩፤
ኤር. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፲፪-፲፱፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፻፳፩፥ ቁ. ፩-፪፡፡

| | |
|---|---|
| ተፈሣሕኩ፡ እስመ ይቤሉኒ፡ ቤተ እግዚአብሔር ነሓውር፤ | ወደእግዚአብሔር ቤት እንኺድ ስላሉኝ ደስ አለኝ፤ |
| ወቆማ እገሪነ ውስተ አዕጻድኪ ኢየሩሳሌም፤ | ኢየሩሳሌም ሆይ! እግሮቻችን በአደባባዮችሽ ቆሙ፤ |
| ኢየሩሳሌምሰ፡ ሕንፅት ከመ ሀገር፡፡ | ኢየሩሳሌምስ፡ እንደተገጠገጠች ከተማ ታንፃለች፡፡ |

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፳፩፥ ቁ. ፲፰-፳፪፡፡

## <u>፰ኛ፡ ሰኞ፥ በቀትሩ፡ ፮ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ዘፀአ. ምዕ. ፴፪፥ ቁ. ፯-፲፭፤
ጥበ. ምዕ. ፩፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፻፳፩፥ ቁ. ፬፡፡

| | |
|---|---|
| እስመ ህየ ዐርጉ አሕዛብ፤ | አሕዛብ፡ ወደዚያ ወጡ፤ |
| ሕዝበ እግዚአብሔር ስምዐ እሥራኤል፤ | የእሥራኤል ምስክሮች፡ የእግዚአብሔር ነገዶችም፤ |
| ከመ ይግነዩ ለስምከ እግዚኦ፡፡ | የእግዚአብሔርን ስም ያመሰግኑ ዘንድ፡፡ |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፲፪-፳፭፡፡

## <u>፱ኛ፡ ሰኞ፥ በቀትር በኋላ፡ ፱ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ዘፍጥ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፩-፳፫፤
ኢሳ. ምዕ. ፵፥ ቁ. ፩-፰፤
ምሳ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፩-፱፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፷፬፥ ቁ. ፭፡፡

| | |
|---|---|
| ሰምዓከነ አምላክነ ወመድኃኒነ፤ | አምላካችን፥ መድኃኒታችን ሆይ! ሰማኸን! |
| ተስፋሆሙ፡ ለኵሎሙ አጽናፈ ምድር፤ | በምድር ዳርቻ ላሉት ኹሉ፡ ተስፋቸው፥ |
| ወለእለሂ ውስተ ባሕር ርሑቅ፡፡ | በሩቅ ባሕር ውስጥ ላሉትም፡ አንተ ነህ፡፡ |

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፳፩፥ ቁ. ፳፫-፳፯፡፡

## ፲ኛ፡ ሰኞ፥ በሠርክ፡ ፲፩ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘፍጥ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፳፬፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፤
ኢሳ. ምዕ. ፳፯፤
ሲራ. ምዕ. ፪፤
ሆሴ.. ምዕ. ፲፬::

ምስባክ፡- መዝ. ፲፪፥ ቁ. ፪-፫::

| | |
|---|---|
| ወትጌዕረኒ ልብየ ኵሎ አሚረ፤ | ልቤ እስከመቼ ኹልጊዜ ያስጨንቀኛል? |
| እስከ ማእዜኑ ይትዔበዩ ጸላእትየ ላዕሌየ፤ | እስከመቼ ጠላቴ፡ በላዬ ይጓደዳል? |
| ነጸርከኒ ወሰማዕከኒ እግዚኦ አምላኪየ:: | አቤቱ አምላኬ፡ አየኸኝ! ሰማኸኝም። |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፶፩-፶፱::

## የማግሰኞ

## ፩ኛ፡ ሰኞ፥ በምሽቱ፡ ፩ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘካ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፩-፯::

ምስባክ፡- መዝ. ፷፩፥ ቁ. ፩-፯::

| | |
|---|---|
| ወባሕቱ ለእግዚአብሔር ትገኒ ነፍስየ፤ | ነገር ግን፡ ነፍሴ፡ ለእግዚአብሔር ትገዛለች፤ |
| እስመ ኀቤሁ ተስፋየ፤ | ተስፋዬ፡ ከእርሱ ዘንድ ናትና፤ |
| እስመ ውእቱ አምላኪየ ወመድኃኒየ:: | እርሱ፡ አምላኬም፥ መድኃኒቴም ነውና:: |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፳፪-፴::

## ፪ኛ፡ ሰኞ፥ በማታው፡ ፫ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ሚል. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፩-፰::

ምስባክ፡- መዝ. ፲፪፥ ቁ. ፫-፬::

| | |
|---|---|
| ነጸርከኒ ወሰማዕከኒ እግዚኦ አምላኪየ፤ | አቤቱ አምላኬ፡ አየኸኝ! ሰማኸኝም። |
| አበርሃሆን ለአዕይንትየ ከመ ኢይኑማ ለመዊት፤ | ለሞት እንዳልተኛ፡ ዓይኖቼን አበራህ! |
| ወከመ ኢይበሉኒ ጸላእትየ፡"ሞእናሁ!" | ጠላቴ፡ "አሸነፍሁት!" እንዳይል:: |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፴፩-፴፭::

## ፫ኛ፡ ማግሰኞ÷ በሌሊቱ፡ ፯ ሰዓት፤

ምንባብ፦ ሆሴ. ምዕ. ፬÷ ቁ. ፲፫-፲፱፡፡
ሆሴ. ምዕ. ፫÷ ቁ. ፩-፯፡፡

ምስባክ፦ መዝ. ፺÷ ቁ. ፪-፫፡፡

| | |
|---|---|
| አምላኪየ ወረዳኢየ÷ ወእትዌከል ቦቱ፤ | በአምላኬና በመሸሸጊያዬ፡ በእርሱ እታመናለሁ፤ |
| እስመ ውእቱ ባልሓኒ፡ እመሥገርት ነዓዊት፤ | እርሱ፡ ከአዳኞች ወጥመድ አድኖኛልና፤ |
| ወእምነገር መደንግፅ፡፡ | ከሚያስደነግጥም ነገር ኹሉ፡፡ |

ወንጌል፦ ሉቃ. ምዕ. ፳፩÷ ቁ. ፴፬-፴፰፡፡

## ፬ኛ፡ ማግሰኞ÷ በነግሁ፡ ፱ ሰዓት፤

ምንባብ፦ ሆሴ. ምዕ. ፲÷ ቁ. ፲፪-፲፫፤
ሆሴ. ምዕ. ፲፩÷ ቁ. ፩-፪፡፡

ምስባክ፦ መዝ. ፴፪÷ ቁ. ፲-፲፩፡፡

| | |
|---|---|
| እግዚአብሔር ይመይጥ ምክሮሙ ለአሕዛብ፤ | እግዚአብሔር የአሕዛብን ምክር ያጠፋል፤ |
| ወይመይጥ ኅሊናሆሙ ለሕዝብ፤ | የሕዝብንም አሳብ ይመልሳል፤ |
| ወምክሩሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም፡፡ | የእግዚአብሔር ምክር ግን፡ ለዘለዓለም ይኖራል፡፡ |

ወንጌል፦ ሉቃ. ምዕ. ፲፩÷ ቁ. ፴፯-፶፪፡፡

## ፭ኛ፡ ማግሰኞ÷ በንጋቱ፡ ፲፩ ሰዓት፤

ምንባብ፦ አሞ. ምዕ. ፭÷ ቁ. ፯-፲፬፡፡

ምስባክ፦ መዝ. ፻፳፩÷ ቁ. ፬-፭፡፡

| | |
|---|---|
| እስመ ህየ ዐርጉ አሕዛብ፤ | አሕዛብ፡ ወደዚያ ወጡ፤ |
| ሕዝበ እግዚአብሔር፡ ስምዐ እሥራኤል፤ | የእግዚአብሔር ሕዝብ፡ የእሥራኤል ምስክር፤ |
| ከመ ይግነዩ ለስምከ ቅዱስ፡፡ | ቅዱስ ስምህን ያመሰግኑ ዘንድ፡፡ |

ወንጌል፦ ማር. ምዕ. ፲፫÷ ቁ. ፴፪-፴፯፤
ማር. ምዕ. ፲፬÷ ቁ. ፩-፪፡፡፡

## ፮ኛ: ማግሰኞ፥ በማለዳው: ፩ ሰዓት፤

ምንባብ:- ዘጸአ. ምዕ. ፲፱፥ ቁ. ፩-፰፤
ኢዮ. ምዕ. ፳፫ እና ፳፬፤
ኢሳ. ምዕ. ፩፥ ፳፩-፴፩::
ሆሴ. ምዕ. ፬፥ ፩-፰::

ምስባክ:- መዝ. ፴፬፥ ቁ. ፬-፯::

| | |
|---|---|
| ኀፍሩ ወኀሰሩ ኵሎሙ | ነፍሴን የሚሹ ኹሉ: ዐፈሩ፤ |
| እለ የኀሥሥዋ ለነፍስየ፤ | ጐሠቈሉም። |
| ገብኡ ድኅሬሆሙ ወተኀፍሩ | ክፉትን በእኔ ላይ ያሰቡ ዐፈሩ፤ |
| እለ መከሩ እኩየ ላዕሌየ፤ | ወደኋላቸውም አሉ። |
| ወኮኑ ከመ ጸበል: ዘቅድመ ገጸ ነፋስ:: | በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ ኾኑ። |

ወንጌል:- ማቴ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፩-፲፮::

## ፯ኛ: ማግሰኞ፥ በጧቱ: ፫ ሰዓት፤

ምንባብ:- ዘዳግ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፲፩-፲፱፤
ሲራ. ምዕ. ፫::

ምስባክ:- መዝ. ፻፲፰፥ ቁ. ፻፶፬-፻፶፯::

| | |
|---|---|
| ፈታሕከ ፍትሕየ ወባልሓኒ፤ | ፍርዴን ፈረድህ፤ አዳንኸም። |
| ወበእንተ ቃልከ አሕየውከኒ፤ | ስለቃልህ ሕያው አደረግኸኝ። |
| ርኁቅ ሕይወት እምኃጥኣን :: | ሕይወት: ከኃጥኣን ሩቅ ናት:: |

ወንጌል:- ማቴ. ምዕ. ፳፫፥ ቁ. ፴፯-፴፱፤
ማቴ. ምዕ. ፳፬፥ ቁ. ፩-፪::

## ፰ኛ: ማግሰኞ፥ በቀትሩ: ፮ ሰዓት፤

ምንባብ:- ሕዝ. ምዕ. ፳፩፥ ቁ. ፫-፲፯፤
ሲራ. ምዕ. ፬::

ምስባክ:- መዝ. ፲፯፥ ቁ. ፲፯-፲፰::

| | |
|---|---|
| ወአድኀነኒ እምፀርየ ጽኑዓን፤ | ከብርቱዎች ጠላቶቼ፥ ከሚጠሉኝም አዳነኝ፤ |
| ወእምጸላእትየ እስመ ይኄይሉኒ፤ | በርትተውብኝ ነበርና፤ ፤ |
| ወበጽሑኒ በዕለተ ምንዳቤየ:: | በመከራዬ ቀን ደረሱብኝ:: |

ወንጌል:- ዮሐ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፲፪-፳::

## ፱ኛ: ማግሰኞ፥ በቀትር በኋላ: ፱ ሰዓት፤

ምንባብ:- ዘፍጥ. ምዕ. ፮፥ ቁ. ፭-፳፪፤
ዘፍጥ. ምዕ. ፯፥ ቁ. ፩-፳፬፤
ዘፍጥ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፩-፳፪፤
ዘፍጥ. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፩-፯፤
ምሳ. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፩-፪፤
ኢሳ. ምዕ. ፵፥ ቁ. ፱-፴፩፤
ዳን. ምዕ. ፯፥ ቁ. ፪-፳፰::

ምስባክ:- መዝ. ፳፬፥ ቁ. ፩-፪::

| | |
|---|---|
| ኀቤከ እግዝኦ አንቃዕዶኩ ነፍስየ አምላኪየ፤ | አቤቱ አምላኬ! ነፍሴን ወዳንተ አነሣለሁ፤ |
| ወኪያከ ተወከልኩ እግዚኦ ወኢይትኀፈር ለዓለም፤ | አቤቱ! በአንተ ታምኛለሁና: ለዘለዓለም አላፍርም፤ |
| ወኢይሥሐቁኒ ጸላእትየ:: | ጠላቶቼ በእኔ አይሣቁብኝ! |

ወንጌል:- ማቴ. ምዕ. ፳፬፥ ቁ. ፫-፴፭::

## ፲ኛ: ማግሰኞ፥ በሠርክ: ፲፩ ሰዓት፤

ምንባብ:- ኢሳ. ምዕ. ፳፱፥ ቁ. ፭-፳፩፤
ኢሳ. ምዕ. ፳፰፥ ቁ. ፲፮-፳፮፤
ምሳ. ምዕ. ፮፥ ቁ. ፳-፴፭፤
ምሳ. ምዕ. ፯፥ ቁ. ፩-፬፤

ምስባክ:- መዝ. ፵፬፥ ቁ. ፮-፯::

| | |
|---|---|
| መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም፤ | አቤቱ! ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው፤ |
| በትረ ጽድቅ፥ ወበትረ መንግሥትከ፤ | የመንግሥትህ በትር: የእውነት በትር ነው፤ |
| አፍቀርከ ጽድቀ፥ ወዐመፃ ጸላእከ:: | አውነትን ወደድህ፥ ዓመፃንም ጠላህ:: |

ወንጌል:- ማቴ. ምዕ. ፳፭፥ ቁ. ፲፬-፵፮::
ማቴ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፩-፪::

## የረቡዕ

## ፩ኛ: ማግሰኞ፥ በምሽቱ: ፩ ሰዓት፤

ምንባብ:- ሕዝ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፲፫-፳፪::

ምስባክ:- መዝ. ፶፰፥ ቁ. ፲፮-፲፯::

| | |
|---|---|
| ረዳኢየ አንተ ወለከ እዜምር ለአምላኪየ፤ | ረዳቴ አንተ ነህ፤ ለአንተ ለአምላኬ እዘምራለሁ፤ |
| እስመ አምላኪየ ወምስካይየ አንተ፤ | አንተ አምላኬ፥ መጠጊያዬም ነህና፤ |
| አምላኪየ ውእቱ ሣህልየ:: | አምላኬ: ምሕረቴም ነህ:: |

ወንጌል:- ማቴ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፩-፲፬::

### ፪ኛ: ማግሰኞ÷ በማታው: ፫ ሰዓት፤

| | |
|---|---|
| ምንባብ:- | አሞ. ምዕ. ፭÷ ቁ. ፲፰-፳፯:: |
| ምስባክ:- | መዝ. ፷፬÷ ቁ. ፬:: |
| ብፁዕ ዘኀረይኮ ወዘተወከፍኮ፤ | አንተ የመረጥከው ብፁዕ ነው፤ |
| ወዘአኅደርኮ ውስተ አዕጻዲከ፤ | በአደባባዮችህ እንዲያድር የተቀበልኸው፤ |
| ጸገብነ እግዚኦ እምበረከተ ቤትከ:: | አቤቱ! ከቤትህ በረከት ጠገብን:: |
| ወንጌል:- | ማቴ. ምዕ. ፳፬÷ ቁ. ፴፮-፶፩:: |

### ፫ኛ: ረቡዕ÷ በሌሊቱ: ፯ ሰዓት፤

| | |
|---|---|
| ምንባብ:- | ኤር. ምዕ. ፲፯÷ ቁ. ፩-፲፫:: |
| ምስባክ:- | መዝ. ፻፩÷ ቁ. ፩-፪:: |
| ሰማዕከኒ እግዚኦ ጸሎትየ፤ | አቤቱ: ጸሎቴን ሰማህ፤ |
| ወበጽሓ ቅድሜከ ገዓርየ፤ | ጩኸቴም ወደአንተ ደረሰ፤ |
| ወኢሜጥከ ገጸከ እምኔየ:: | ፊትህን ከእኔ አልመለስህም። |
| ወንጌል:- | ማቴ. ምዕ. ፳፭÷ ቁ. ፩-፲፫:: |

### ፬ኛ: ረቡዕ÷ በነግሁ: ፱ ሰዓት፤

| | |
|---|---|
| ምንባብ:- | ሆሴ. ምዕ. ፱÷ ቁ. ፲፬-፲፯:: |
| ምስባክ:- | መዝ. ፳፪÷ ቁ. ፳-፳፩:: |
| አድኅንካ እምኵናት ለነፍስየ፤ | ነፍሴን  ከሰይፍ አዳንሃት፤ |
| ወእምእደ ከለባት ለብሕቱትየ፤ | ብቸኝነቴንም: ከውሾች እጅ፤ |
| አድኅንከኒ እምአፈ አንበሳ፤ | ከአንበሳ አፍ አዳንኸኝ። |
| ወንጌል:- | ማቴ. ምዕ. ፳፫÷ ቁ. ፳፫-፴፯:: |

### ፭ኛ: ረቡዕ÷ በንጋቱ: ፲፩ ሰዓት፤

| | |
|---|---|
| ምንባብ:- | ጥበ. ምዕ. ፭:: |
| ምስባክ:- | መዝ. ፶፯÷ ቁ. ፩-፪:: |
| ተሣሃልከኒ እግዚኦ ተሣሃልከኒ! | ማርኸኝ! አቤቱ ማርኸኝ! |
| እስመ ኪያከ ተወከለት ነፍስየ፤ | ነፍሴ በአንተ ተማምናለች፤ |
| ወተወከልኩ በጽላሎተ ክነፊከ:: | በክንፎችህ ጥላ እታመናለሁ:: |
| ወንጌል:- | ዮሐ. ምዕ. ፲፩÷ ቁ. ፶፭-፶፯:: |

## ፮ኛ፡ ረቡዕ÷ በማለዳው፡ ፩ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘጸአ. ምዕ. ፲፯÷ ቁ. ፩-፯፤
ኢሳ. ምዕ. ፪÷ ቁ. ፩-፲፩፤
ምሳ. ምዕ. ፫÷ ቁ. ፩-፭::
ሆሴ. ምዕ. ፭÷ ቁ. ፲፫-፲፭::

ምስባክ፡- መዝ. ፹፪÷ ቁ. ፭-፮::

| | |
|---|---|
| እስመ ተማከሩ ኅቡረ ወዐረዩ፤ | አንድ ኾነው፡ በአንተ ላይ ተማከሩ፤ |
| ላዕሌከ ተሰካተዩ ወተካየዱ፤ | በአንተ ላይ ቃል ኪዳን አደረጉ፤ |
| ተዓይኒሆሙ ለኤዶምያስ ወለእስማኤላውያን:: | የኤዶማውያንና የእስማኤላውያን ድንኳኖች÷ |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፲፩÷ ቁ. ፵፯-፶፬::

## ፯ኛ፡ ረቡዕ÷ በጧቱ፡ ፫ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘጸአ. ምዕ. ፲፫÷ ቁ. ፲፯-፳፪፤
ሲራ. ምዕ. ፳፪::

ምስባክ፡- መዝ. ፵÷ ቁ. ፮-፯::

| | |
|---|---|
| ይባእ ወይርአይ ዘከንቶ ይነብብ፤ | እኔን ለማየት ቢገባ፡ ከንቱን ይናገራል፤ |
| ልቡ አስተጋብአ ኃጢኣተ ላዕሌሁ፤ | ልቡ፡ ኃጢኣትን በላዩ ሰበሰበለት፤ |
| ይወጽእ አፍኣ ወይትናገር ወየኀብር ላዕሌየ:: | ወደሜዳም ይወጣል፤ በላዬም በመተባበር ይናገራል:: |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፳፪÷ ቁ. ፩-፮::

## ፰ኛ፡ ረቡዕ÷ በቀትሩ፡ ፮ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘፀአ. ምዕ. ፲፬÷ ቁ. ፲፫-፴፩፤
ሲራ. ምዕ. ፳፫::

ምስባክ፡- መዝ. ፵÷ ቁ. ፭-፮::

| | |
|---|---|
| ጸላእትየሰ እኩየ ይቤሉ ላዕሌየ፤ | ጠላቶቼ በላዬ ክፉን ይናገራሉ፤ |
| ማእዜ ይመውት ወይሠዓር ስሙ፤ | መቼ ይሞታል? ስሙስ መቼ ይሻራል? ይላሉ፤ |
| ይባእ ወይርአይ ዘከንቶ ይነብብ:: | እኔን ለማየት ቢገባ፡ ከንቱን ይናገራል:: |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፯÷ ቁ. ፴፮-፶::

## ፱ኛ፡ ረቡዕ፥ በቀትር በኋላ፡ ፱ ሰዓት፤

ምንባብ፦ ዘፍጥ. ምዕ. ፳፬፥ ቁ. ፩-፱፤
ዘኍል. ምዕ. ፳፥ ቁ. ፩-፲፫፤
ምሳ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፲-፴፫፡፡

ምስባክ፦ መዝ. ፹፪፥ ቁ. ፪-፫፡፡

| | |
|---|---|
| እስመ ናሁ ወውዑ ፀርከ፤ | እነሆ፡ ጠላቶችህ ጮኸዋልና፤ |
| ወአንሥኡ ርእሶሙ ጸላእትከ፤ | የሚጠሉህም ራሳቸውን አንሥተዋልና፡ |
| ወተጓሕለውዎሙ ምክረ ለሕዝብከ፡፡ | ሕዝብህን በምክር ሸነገሏቸው፡፡ |

ወንጌል፦ ማር. ምዕ. ፲፬፥ ቁ. ፩-፲፩፡፡

## ፲ኛ፡ ረቡዕ፥ በሠርክ፡ ፲፩ ሰዓት፤

ምንባብ፦ ኢሳ. ምዕ. ፶፰፥ ቁ. ፩-፲፬፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፱፥ ቁ. ፩-፳፤

ምስባክ፦ መዝ. ፮፥ ቁ. ፪-፫፡፡

| | |
|---|---|
| ተሣሃልከኒ እግዚኦ እስመ ድውይ አነ፤ | በሽተኛ ነበርሁ፤ አቤቱ ማርኸኝ! |
| ወፈወስከኒ እስመ ተሀውካ አዕፅምትየ፤ | አጥንቶቼ ታውከው ነበር፤ ፈወስኸኝ፤ |
| ነፍስየኒ ተሀውከት ፈድፋደ፡፡ | ነፍሴ እጅግ ታውካ ነበር። |

ወንጌል፦ ዮሐ. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፳፯-፴፮፡፡

## የሐሙስ

## ፩ኛ፡ ረቡዕ፥ በምሽቱ፡ ፩ ሰዓት፤

ምንባብ፦ ሕዝ. ምዕ. ፵፯፥ ቁ. ፩-፲፬፡፡

ምስባክ፦ መዝ. ፷፰፥ ቁ. ፩-፪፡፡

| | |
|---|---|
| አድኅንከኒ እግዚኦ እስመ በጽሓኒ ማይ እስከ ነፍስየ፤ | አቤቱ፥ ውኃ እስከነፍሴ ደርሶብኛ፡ አዳንኸኝ። |
| ጠጋዕኩ ውስተ ዕሙቅ ቀላይ ወኃይል አልብየ፤ | በጥልቅ ረግረግ ጠለቅሁ፥ ዓቅምምም አጣሁ፤ |
| በጻሕኩ ውስተ ማዕምቀ ባሕር ወዐውሎ አስጠመኒ፡፡ | ከባሕሩ ጥልቀት ደረስሁ፤ ማዕበሉ አሰጠመኝ፡፡ |

ወንጌል፦ ዮሐ. ምዕ. ፲፥ ቁ. ፲፯-፳፩፡፡

<u>፪ኛ፡ ረቡዕ፥ በማታው፡ ፫ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- አሞ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፪-፲፫::

ምስባክ፡- መዝ. ፻፴፱፥ ቁ. ፩-፪::

| | |
|---|---|
| አድኅንከኒ እግዚኦ እምብእሲ እኩይ፤ | አቤቱ፥ ከክፉ ሰው አዳንኸኝ! |
| ወእምሰብእ ዐማፂ ባልሓኒ፤ | ከዐመፀኛ ሰው ጠበቅኸኝ! |
| እለ ዐምፃ መከሩ በልቦሙ:: | በልባቸው፡ ዐምፅን ከሸመቁ:: |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፩-፲፩::

<u>፫ኛ፡ ሐሙስ፥ በሌሊቱ፡ ፯ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- አሞ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፲፩::

ምስባክ፡- መዝ. ፷፫፥ ቁ. ፭::

| | |
|---|---|
| ወአጽንዑ ሎሙ ነገረ እኩየ፤ | ለእነርሱ ለራሳቸው፡ ክፉ ነገርን አጸኑ፤ |
| ወተማከሩ ይኅብኡ ሎሙ መሥገርተ፤ | ወጥመድን ይሠውሩ ዘንድ ተማከሩ፤ |
| ወይቤሉ፡ "አልቦ ዘይሬእየነ!" | "የሚያየን የለም!" ይላሉም:: |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፴፯-፵፫::

<u>፬ኛ፡ ሐሙስ፥ በነግሁ፡ ፱ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ሕዝ. ምዕ. ፳፥ ቁ. ፴-፴፫::

ምስባክ፡- መዝ. ፯፥ ቁ. ፩-፪::

| | |
|---|---|
| እግዚኦ አምላኪየ፡ ብከ ተወከልኩ ኢገደፍከኒ፤ | አቤቱ፥ አምላኬ! በአንተ ታምኛለሁና አልተውኸኝም፤ |
| ወአድኅንከኒ እምኵሎሙ እለ ሮዱኒ ወባልሃኒ! | ከሚያሳድዱኝ ኹሉ አዳንኸኝ፤ አወጣኸኝ፤ |
| ከመ ኢይምሥጥዋ፡ ከመ አንበሳ ለነፍስየ:: | ነፍሴን፡ እንደአንበሳ ነጥቀው እንዳይሰብሩዋት:: |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፲፥ ቁ. ፳፯-፴፱::

<u>፫ኛ፡ ሐሙስ፥ በንጋቱ፡ ፲፩ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ኤር. ምዕ. ፳፥ ቁ. ፬-፱::

ምስባክ፡- መዝ. ፷፩፥ ቁ. ፩-፪::

| | |
|---|---|
| እስመ ኀቤሁ መድኃኒትየ፤ | መድኃኒቴ ከእርሱ ዘንድ ናትና፤ |
| እስመ ውእቱ አምላኪየ ወመድኃኒየ፤ | እርሱ አምላኬ፡ መድኃኒቴም ነውና፤ |
| ወውእቱ ረዳኢየ ወኢይትሀወክ ለዝሉፉ:: | እርሱ ረዳቴ ስለኾነ፡ ምንጊዜም አልታወክም:: |

ወንጌል፡- ዮሐ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፴፬-፵::

## ፮ኛ፡ ሓሙስ÷ በማለዳው፡ ፩ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘጸአ. ምዕ. ፲፯÷ ቁ. ፰-፲፮፤
የሓዋ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፲፫-፳፤

ምስባክ፡- መዝ. ፶፬÷ ቁ. ፳፩-፳፪::

| | |
|---|---|
| ወጽሕደ እምቅብዕ ነገሩ፤ | ቃሎቹ፡ ከዘይት ይልቅ ለሰለሱ፤ |
| እሙንቱሰ ማዕበል ያሰጥሙ፤ | እነርሱም፡ የሚያስጥም ማዕበል ናቸው፤ |
| ግድፍ ላዕለ እግዚአብሔር ኀሊናከ | ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል! |
| ወውእቱ ይሴስየከ:: | እርሱም፡ ይደግፍሃል:: |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፳፪÷ ቁ. ፩-፲፬::

## ፯ኛ፡ ሓሙስ÷ በጧቱ፡ ፫ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ዘጸአ. ምዕ. ፴፪÷ ቁ. ፴-፴፫፤
ዘጸአ. ምዕ. ፴፫÷ ቁ. ፩-፫፤
ሚክ. ምዕ. ፪÷ ቁ. ፫-፲፫፤
ሲራ. ምዕ. ፳፬::

ምስባክ፡- መዝ. ፺፫÷ ቁ. ፳፩-፳፪::

| | |
|---|---|
| ወይንዕዋ ለነፍሰ ጻድቅ፤ | የእውነተኛን ሰው ነፍስ ያደቡባታል፤ |
| ወይኬንን ደመ ንጹሓ፤ | በንጹሕ ደምም ይፈርዳሉ፤ |
| ወኮነኒ እግዚአብሔር ጸወንየ:: | በዚህ ጊዜ፡ እግዚአብሔር መጠጊያ ኾነኝ:: |

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፳፮÷ ቁ. ፲፯-፲፱::

## ፰ኛ፡ ሓሙስ÷ በቀትሩ፡ ፮ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ኤር. ምዕ. ፯÷ ቁ. ፫-፲፫፤
ሕዝ. ምዕ. ፳÷ ቁ. ፴፱-፵፬፤
ሚክ. ምዕ. ፪÷ ቁ. ፯-፲፫፤
ሚክ. ምዕ. ፫÷ ቁ. ፩-፰፤
ሶፎ. ምዕ. ፩÷ ቁ. ፯-፲፰፤
ሲራ. ምዕ. ፲፪::

ምስባክ፡- መዝ. ፴÷ ቁ. ፲፫-፲፬::

| | |
|---|---|
| እስመ ሰማዕኩ ድምፀ ብዙኃን እለ ዐገቱኒ ዐውድየ፤ | ዙርያዬን የከበቡኝን የብዙዎችን ድምፅ ሰማሁ፤ |
| ሶበ ተጋብኡ ኅቡረ ላዕሌየ፤ | በእኔ ላይ በአንድነት ተሰብስበው÷ |
| ወተማከሩ ይምሥጥዋ ለነፍስየ:: | ነፍሴን ሊያጠፉ ሲማከሩ:: |

ወንጌል፡- ማር. ምዕ. ፲፬÷ ቁ. ፲፪-፲፮::

## ፱ኛ፡ ሓሙስ፥ በቀትር በኋላ፡ ፱ ሰዓት፤

ምንባብ፡-
ዘፍጥ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፩-፲፱፤
ኢሳ. ምዕ. ፴፩፥ ቁ. ፩-፯፤
ኢዮ. ምዕ. ፳፯፥ ቁ. ፩-፳፫፡፡
ኢዮ. ምዕ. ፳፰፥ ቁ. ፩-፲፫፤
ሚል. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፱-፲፬፤
ሚል. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፩-፰፡፡

ምስባክ፡-
መዝ. ፳፪፥ ቁ. ፩-፪፡

| | |
|---|---|
| እግዚአብሔር ይሬእየኒ ወአልቦ ዘየኀጥአኒ፤ | እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝም የለም፤ |
| ውስተ ብሔር ሥዑር ህየ የኀድረኒ፤ | ልምላሜን በተጐናጸፈ ምድር ያሳድረኛል፤ |
| ውኅበ ማየ ዕረፍት ሐፀነኒ፡፡ | ውኃ ወዳለበትም መርቶ ያሳርፈኛል፡፡ |

ወንጌል፡-
ሉቃ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፯-፲፫፡፡

## የኀፅበተ እግር

ምንባብ፡-
ዘፍጥ. ምዕ. ፲፰፥ ቁ. ፩-፴፫፤
ዘጸአ. ምዕ. ፲፬፥ ቁ. ፳፱-፴፩፤
ኢያ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፲፫-፲፯፤
ኢሳ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፪-፮፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፭፥ ቁ. ፩-፲፫፤
ሕዝ. ምዕ. ፲፩፥ ቁ. ፲፯-፳፩፤
ሕዝ. ምዕ. ፵፯፥ ቁ. ፪-፱፤
መዝ. ምዕ. ፶፤
መዝ. ምዕ. ፻፤
መዝ. ምዕ. ፻፬፤
መዝ. ምዕ. ፻፲፤
መዝ. ምዕ. ፻፲፫፤
መዝ. ምዕ. ፴፰፤
፩ጢሞ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፱-፲፮፤
፩ጢሞ. ምዕ. ፭፥ ቁ. ፩-፲፤
፩ጴጥ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፰-፳፤
የሓዋ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፳፮-፵፡፡

ምስባክ፡-
መዝ. ፶፥ ቁ. ፯-፰፡፡

| | |
|---|---|
| ትነዝህኒ በአዛብ ወእነጽሕ፤ | በሂሶጵ ትረጨኛለህ፤ እነጻማለሁ፤ |
| ተኀጽበኒ እምበረድ ወእጻዐዱ፤ | ታጥበኛለህ፤ ከበረዶም ይልቅ፡ ነጭ እኾናለሁ፤ |
| ታሰምዓኒ ትፍሥሕተ ወሓሤተ፡፡ | ሓሤትንና ደስታንም ታሰማኛለህ፡፡ |

ወንጌል፡-
ዮሓ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፩-፳፡፡

# የቍርባን

ምንባብ፡- ፩ቆሮ. ምዕ. ፲፩፥ ቁ. ፳፫-፴፬፤
፩ጴጥ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፲፱-፳፫፤
የሐዋ. ምዕ. ፲፥ ቁ. ፴፬-፵፫፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፳፪፥ ቁ. ፭-፮፡፡

| | |
|---|---|
| ወሠራዕከ ማዕደ በቅድሜየ፤ | በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ፤ |
| በአንጻሪሆሙ ለእለ ይሣቅዩኒ፤ | በጠላቶቼ ፊት ለፊት፤ |
| ወአጽሐድከ በቅብዕ ርእስየ፡፡ | ራሴን በዘይት ቀባህ፡፡ |

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፳-፴፡፡

## ፲ኛ፡ ሐሙስ፥በሠርክ፡ ፲፩ ሰዓት፤

ምንባብ፡- መዝ. ምዕ. ፻፶፤
ኤር. ምዕ. ፴፩፥ ቁ. ፲፭-፳፮፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፪፥ ቁ. ፲፫-፲፭፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፫፥ ቁ. ፩-፲፪፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፬፥ ቁ. ፩-፰፤
ኢሳ. ምዕ. ፴፩፥ ቁ. ፩-፱፤
ኢሳ. ምዕ. ፴፪፥ ቁ. ፩-፳፤
ኢሳ. ምዕ. ፴፫፥ ቁ. ፩-፲፡፡

# የዓርብ፥ የስቅለት

## ፩ኛ፡ ሐሙስ፥ በምሽቱ፡ ፩ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ኤር. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፲፯-፳፪፤
ኤር. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፩-፫፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፻፩፥ ቁ. ፩-፪፡፡

| | |
|---|---|
| ሰማዕከኒ እግዚኦ ጸሎትየ፤ | አቤቱ፡ ጸሎቴን ሰማህ፤ |
| ወበጽሐ ቅድሜከ ገዓርየ፤ | ጩኸቴም ወደአንተ ደረሰ፤ |
| ወኢሜጥከ ገጸከ እምኔየ፡፡ | ፊትህን ከእኔ አልመለስህም። |

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፳-፳፱፤
ማር. ምዕ. ፲፬፥ ቁ. ፲፯-፳፫፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፲፬-፴፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፳፩-፴፰፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፬-፲፯፡፡

፪ኛ፡ ሓሙስ፥ በማታው፡ ፫ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ሕዝ. ምዕ. ፳፥ ቁ. ፴፱-፵::

ምስባክ፡- መዝ. ፻፰፥ ቁ. ፩-፪::

| | |
|---|---|
| እግዚኦ ኢተጸመምከኒ ስእለትየ፤ | አቤቱ፥ ልመናዬን ከመስማት ዝም አላልህም። |
| እስመ አፈ ዐማፂ፥ ወአፈ ኃጥእ፡ | የዐመፀኛ አፍና የኃጢአተኛ አፍ በላዬ |
| አብቀዉ ላዕሌየ፤ | ተላቅቀውብኛልና፤ |
| ወነበቡ ላዕሌየ በልሳነ ዐመፃ:: | በዐመፅ አንደበት፡ በላዬ ተናገሩ:: |

ወንጌል፡-
ማቴ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፴-፴፭፤
ማር. ምዕ. ፲፬፥ ቁ. ፳፮-፴፩፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፴፩-፴፱፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፰፥ ቁ. ፩-፱፤

፫ኛ፡ ዓርብ፥ በሌሊቱ፡ ፮ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ሕዝ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፳፫-፳፰::

ምስባክ፡- መዝ. ፷፰፥ ቁ. ፲፰-፲፱::

| | |
|---|---|
| ነጸራ ለነፍስየ ወአድኅና፤ | ነፍሴን ተመልክቶ፡ ተቤዣት! |
| ወአድኅነኒ በእንተ ጸላእትየ፤ | ስለጠላቶቼም አዳነኝ፤ |
| ለሊከ እግዚኦ፡ ተአምር ጽዕለትየ:: | አንተ ስድቤን ታውቃለህና:: |

ወንጌል፡-
ማቴ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፴፮-፵፮፤
ማር. ምዕ. ፲፬፥ ቁ. ፴፪-፵፪፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፵-፵፮፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፰፥ ቁ. ፫-፱::

፬ኛ፡ ዓርብ፥ በነግሁ፡ ፱ ሰዓት፤

ምንባብ፡- ኤር. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፯-፲፩::
ሕዝ. ምዕ. ፳፭፥ ቁ. ፩-፲፯::

ምስባክ፡- መዝ. ፳፯፥ ቁ. ፫-፬::

| | |
|---|---|
| እለ ይትናገሩ ሰላመ ምስለ ቢጾሙ፤ | ከባልንጀራቸው ጋር ሰላም ስለሚናገሩ፤ |
| ወእኩይ ውስተ ልቦሙ፤ | ክፋት በልባቸው እያለ፤ |
| ሀብኮሙ በከመ ምግባሮሙ:: | እንደሥራቸው ሰጠሃቸው:: |

ወንጌል፡-
ማቴ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፵፯-፶፰፤
ማር. ምዕ. ፲፬፥ ቁ. ፵፫-፶፬፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፵፯-፶፭፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፰፥ ቁ. ፲-፲፬::

<u>፭ኛ፡ ዓርብ፥ በንጋቱ፡ ፲፩ ሰዓት፤</u>

| | | |
|---|---|---|
| | ምንባብ፡- | ኢሳ. ምዕ. ፳፯፥ ቁ. ፲፩-፲፫፤<br>ኢሳ. ምዕ. ፳፰፥ ቁ. ፩-፲፭፡፡ |
| | ምስባክ፡- | መዝ. ፪፥ ቁ. ፩-፪፡፡ |
| ለምንት አንገለጉ አሕዛብ፤ | | አሕዛብ፡ ለምን ያጒረመርማሉ? |
| ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ፤ | | ወገኖችስ፡ ለምን ከንቱ ነገርን ይናገራሉ? |
| ወተንሥኡ ነገሥተ ምድር፡፡ | | የምድር ነገሥታት ተነሡ፡፡ |
| | ወንጌል፡- | ማቴ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፶፱-፸፭፤<br>ማር. ምዕ. ፲፬፥ ቁ. ፶፭-፸፪፤<br>ሉቃ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፶፮-፷፬፤<br>ዮሐ. ምዕ. ፲፰፥ ቁ. ፲፭-፳፯፡፡ |

<u>፮ኛ፡ ዓርብ፥ በማለዳው፡ ፩ ሰዓት፤</u>

| | | |
|---|---|---|
| | ምንባብ፡- | ዘዳግ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፲፱-፳፤<br>ዘዳግ. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፩-፳፬፤<br>ኢሳ. ምዕ. ፩፥ ፩-፱፡፡<br>ኢሳ. ምዕ. ፴፫፥ ቁ. ፭-፳፪፤<br>ኤር. ምዕ. ፳፥ ቁ. ፩-፲፰፤<br>ኤር. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፩-፰፤<br>ጥበ. ምዕ. ፩፡፡<br>ዘካ. ምዕ. ፲፩፥ ቁ. ፲፩-፲፬፤<br>ሚክ. ምዕ. ፯፥ ቁ. ፩-፰፤<br>አሞ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፩-፲፮፤<br>አሞ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፯፤<br>ሆሴ. ምዕ. ፲፥ ቁ. ፫-፰፡፡ |
| | ምስባክ፡- | መዝ. ፴፬፥ ቁ. ፲፩-፲፪፡፡ |
| ተንሥኡ ላዕሌየ ሰማዕተ ዐመፃ፤ | | የዐመፃ ምስክሮች ተነሡብኝ፤ |
| ወዘኢየአምር ነበቡ ላዕሌየ፤ | | የማላውቀውንም፡ በእኔ ላይ ተናገሩ፤ |
| ፈደዩኒ እኪተ ህየንተ ሠናይት፡፡ | | ስለበጎ ክፋትን መለሱልኝ፡፡ |
| | ወንጌል፡- | ማቴ. ምዕ. ፳፯፥ ቁ. ፩-፲፬፤<br>ማር. ምዕ. ፲፭፥ ቁ. ፩-፭፤<br>ሉቃ. ምዕ. ፳፪፥ ቁ. ፷፭-፸፩፤<br>ዮሐ. ምዕ. ፲፰፥ ቁ. ፳፰-፵፡፡ |

<u>፯ኛ፡ ዓርብ፥ በጧቱ፡ ፫ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- መዝ. ምዕ. ፴፬፡፡
ዘፍጥ. ምዕ. ፵፰፥ ቁ. ፩-፳፪፤
ኢሳ. ምዕ. ፷፫፥ ቁ. ፩-፲፱፤
ኢሳ. ምዕ. ፷፬፥ ቁ. ፩-፬፤
ኢሳ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፰-፲፮፡፡
ኢሳ. ምዕ. ፶፥ ቁ. ፬-፲፩፤
ኢሳ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፭-፲፭፤
ሚክ. ምዕ. ፯፥ ቁ. ፱-፳፤
ኢዮ. ምዕ. ፳፱፥ ቁ. ፩-፳፭፤
ኢዮ. ምዕ. ፴፥ ቁ. ፩-፲፬፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፳፩፥ ቁ. ፲፮-፲፯፡፡

| | |
|---|---|
| ዐገቱኒ ከለባት ብዙኃን፤ | ብዙ ውሾች ከብበውኛል፤ |
| ወአኀዙኒ ማኅበሮሙ ለእኩያን፤ | የክፉዎች ጉባኤም ያዘኝ፤ |
| ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ፡፡ | እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፡፡ |

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፳፯፥ ቁ. ፲፭-፳፮፤
ማር. ምዕ. ፲፭፥ ቁ. ፮-፲፭፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፫፥ ቁ. ፲፫-፳፭፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፱፥ ቁ. ፩-፲፪፡፡

<u>፰ኛ፡ ዓርብ፥ በቀትሩ፡ ፮ ሰዓት፤</u>

ምንባብ፡- ዘኁ. ምዕ. ፳፩፥ ቁ. ፩-፱፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፫፥ ቁ. ፯-፲፪፤
ኢሳ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፩-፲፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፥ ቁ. ፲-፲፩፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፩፥ ቁ. ፩-፮፡፡
አሞ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፰-፲፬፤
አሞ. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፩-፲፭፤
ሕዝ. ምዕ. ፴፯፥ ቁ. ፲፭-፳፪፤
ገላ. ምዕ. ፮፥ ቁ. ፲፬-፲፯፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፳፩፥ ቁ. ፲፮-፲፯፡፡

| | |
|---|---|
| ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ፤ | እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፤ |
| ወኈለቁ ኵሉ አዕፅምትየ፤ | አጥንቶቼ ኹሉ ተቈጠሩ፤ |
| እሙንቱሰ ጠይቆሙ ወተዐወሩኒ፡፡ | እነርሱም አዩኝ፥ ተመለከቱኝም፡፡ |

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፳፯፥ ቁ. ፳፯-፵፭፤
ማር. ምዕ. ፲፭፥ ቁ. ፲፮-፴፫፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፫፥ ቁ. ፳፯-፵፬፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፱፥ ቁ. ፲፫-፳፯፡፡

## ፱ኛ፡ ዓርብ፥ በቀትር በኋላ፡ ፱ ሰዓት፤

ምንባብ፦

ኢያ. ምዕ. ፭፥ ቁ. ፲-፲፪፤
ሩት ምዕ. ፪፥ ቁ. ፲፩-፲፬፤
ኤር. ምዕ. ፲፰፥ ቁ. ፲፰-፳፫፤
ኤር. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፩-፲፫፤
ኢሳ. ምዕ. ፳፬፥ ቁ. ፩-፳፫፤
ኢሳ. ምዕ. ፳፭፥ ቁ. ፩-፲፪፤
ኢሳ. ምዕ. ፳፮፥ ቁ. ፩-፳፤
ዘካ. ምዕ. ፲፬፥ ቁ. ፭-፲፩::
ኢዮ. ምዕ. ፲፮፥ ቁ. ፩-፳፪፤
ፊልጵ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፩-፲፰::

ምስባክ፦ መዝ. ፷፰፥ ቁ. ፳፩-፳፪::

| | |
|---|---|
| ወወደዩ ሐሞተ ውስተ መብልዕየ፤ | በመብሌ ውስጥ ሐሞትን ጨመሩ፤ |
| ወአስተዩኒ ብሒአ ለጽምእየ፤ | ለጥማቴም ሆምጣጤን አጠጡኝ፤ |
| ኮነት ማእዶሙ መሥገርተ በቅድሜሆሙ:: | ገበታቸው፡ በፊታቸው፡ ወጥመድ ኾነችባቸው:: |

ወንጌል፦

ማቴ. ምዕ. ፳፯፥ ቁ. ፵፮-፶፤
ማር. ምዕ. ፲፭፥ ቁ. ፴፬-፴፯፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፫፥ ቁ. ፵፭-፵፮፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፱፥ ቁ. ፳፰-፴::

## ፲ኛ፡ ዓርብ፥ በሠርክ፡ ፲፩ ሰዓት፤

ምንባብ፦

ዘጸአ. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፩-፲፬፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፩፥ ቁ. ፱-፳፫፤
ኢሳ. ምዕ. ፶፪፥ ቁ. ፩-፲፭፤
ሶፎ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፭-፲፭፤
ሶፎ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፰::

ምስባክ፦ መዝ. ፻፵፪፥ ቁ. ፮-፯::

| | |
|---|---|
| አንሥእኩ እደውየ ኀቤከ፤ | እጆቼን ወደአንተ ዘረጋሁ፤ |
| ነፍስየኒ፡ ከመ ምድረ በድው ጸምአተከ፤ | ነፍሴም እንደምድረ በዳ፡ አንተን ተጠማች፤ |
| ፍጡነ ሰምዓከኒ እግዚኦ ኀለፈት ነፍስየ:: | አቤቱ ነፍሴ አልቃለችና፡ ፈጥነህ ስማኸኝ:: |

ወንጌል፦

ማቴ. ምዕ. ፳፯፥ ቁ. ፶፩-፶፮፤
ማር. ምዕ. ፲፭፥ ቁ. ፴፰-፵፩፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፫፥ ቁ. ፵፯-፵፱፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፱፥ ቁ. ፴፩-፴፯::

**፲፩ኛ፡ ዓርብ፥ በሠርክ፡ ፲፪ ሰዓት፤**

ምንባብ፦ ሰቆ. ኤር. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፳፮፤
መኃ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፲፬-፲፮፤ ፭፥ ቁ. ፩-፪።

ምስባክ፦ መዝ. ፻፵፪፥ ቁ. ፫-፬።

| | |
|---|---|
| እስመ ሮዳ ጸላኢ ለነፍስየ፤ | ጠላት ነፍሴን አሳድዷታል፤ |
| ወአኅሠራ ውስተ ምድር ለሕይወትየ፤ | ሕይወቴንም በምድር ውስጥ አጐሣቍሏታል፤ |
| ወአንበሩኒ ውስተ ጽልመት ከመ ምውተ ትካት። | ቀድሞ እንደሞተ ሰው፡ በጨለማ አኑሮኛል። |

ወንጌል፦ ማቴ. ምዕ. ፳፯፥ ቁ. ፶፯-፷፩፤
ማር. ምዕ. ፲፭፥ ቁ. ፵፪-፵፯፤
ሉቃ. ምዕ. ፳፫፥ ቁ. ፶-፶፮፤
ዮሐ. ምዕ. ፲፱፥ ቁ. ፴፰-፵፪።

**፲፪ኛ፡ ዓርብ፥ በሠርክ፡ ፲፪ ሰዓት፡ ከእግዚኦታ በኋላ፤**

ምንባብ፦ ዳን. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፴፤
ሶስና፤
መዝ. ፻፶፤
ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ፤
ዘጸአ. ምዕ. ፲፭፥ ቁ. ፩-፲፱፤
ንዑስ አነ እምአኃውየ፤
መዝ. ፻፳፤
መዝ. ፩።

## ዕለተ ሰንበት፡ ዘአክበራ እግዚእነ በዕረፍቱ።

ምንባብ፦ ራእየ ዮሐንስን በሙሉ።

\+ \+ \+